# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ | 84ኛ ዓመት ቁጥር 062 ኅዳር 2 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!











# “ቤኑና መንደር አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ተቋቁሞ ሀገርን በትጋት ለመለወጥ ትምህርት የሚወሰድበት ነው”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ቤኑና መንደር አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ተቋቁሞ ሀገርን በትጋት ለመለወጥ ትምህርት የሚወሰድበት ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በበሰቃ ሀይቅ ላይ የተገነባውን ቤኑና መንደርን መርቀው ከፍተዋል።

ቤኑና መንደር በበሰቃ ሀይቅ ዳርቻ እጅግ ዘመናዊ መኝታ ክፍሎች፣ አዳራሽ፣ ሲኒማ ቤት፣ የመዝናኛ ስፍራዎች፣ ስፓ፣ እንዲሁም የፍራፍሬ ልማት እና የሌማት ትሩፋትን አካቶ የያዘ ነው።

የመንደሩ ግንባታም ባህላዊ የኪነ-ህንጻ ጥበብን ከዘመናዊ ግንባታ ጋር አቀናጅቶ የያዘ ሲሆን፤ ለአካባቢው ተጨማሪ የቱሪዝም አቅም የፈጠረ ውብ መዳረሻ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መንደሩን መርቀው በከፈቱበት ወቅት ባስተላለፉት መልዕክት፤ ቤኑና መንደር ይቻላልን በዓይናችን ያየንበት ነው ብለዋል።

አካባቢው በጣም አስቸጋሪ የአየር ጠባይና መልክዓ ምድር እንዳለው ጠቅሰው፤ ይህን በመቋቋም ውብ ገጽታ ያለውን መንደር እውን ማድረግ ተችሏል ነው ያሉት።

ይህም ፈተና ኢትዮጵያን ከመቀየር እንደማያቆመን ዳግም ያረጋገጥንበት ነው ሲሉም ተናግረዋል።

“ቤኑና መንደር አስቸጋሪ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# ድህረ ምርት ብክነት- የምግብ ዋስትና ስጋት

ሳሙኤል ወንደሰን

ዜና ትንታኔ

የዓለም የምግብና የእርሻ ድርጅት (FAO) በኢትዮጵያ ከ30 በመቶ በላይ የሚሆነው የግብርና ምርት እንደሚባክን አሳውቋል።

ድህረ ምርት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር)

## የግል አልሚዎች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች የሚፈታ አሠራር ተዘርግቷል

ገጽ 4

# የገጠር ኮሪደር ተምሳሌት

ነፃነት አለሙ

በከተሞች የተጀመረውን የኮሪደር ልማት ሥራ በገጠሮችም ለማከናወን መታቀዱን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መግለጻቸው የሚታወስ ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳስረዱት፤ የገጠር ኮሪደር ማለት የእያንዳንዱን አርሶ አደር ቤት እና የአኗኗር ዘዬ መቀየር እና በቤተሰብ ደረጃ የአርሶ አደሩን ሕይወት በመቀየር እንደ ሀገር የታሰበውን ብልጽግና ለማረጋገጥ ያለመ ነው።

የገጠር ኮሪደር ልማት ምን ሊመስል ይችላል የሚለውን የተለያዩ መገናኛ ብዙኃን በምስል ሲያስተላልፉ ከተጠቀሟቸው ምስሎች ደግሞ አንዱና ዋነኛው በጉራጌ አካባቢ የሚገኙ ባህላዊ አሠራሮች ታዋቂው የጀፎረ መንገድ ይገኝበታል።

የባህል ባለሙያ የሆኑት አቶ ተስፋዬ ጎይቴ በጥናታዊ ጽሑፋቸው ጀፎረ በመባል የሚጠራ አውራ ጎዳና በጉራጌ አካባቢ የውበትና የንጽህና መገለጫ መሆኑን ያስረዳሉ።

ጀፎረ የጉራጌ ምድር መለያው፣ መታወቂያውና መገለጫ ቅርሱ ነው የሚሉት ባለሙያው፤ በግራና በቀኝ በትይዩ በሚገኙ መንደሮች መካከል ለጥ ብለው የሚታዩ፣ እንደዘመናዊ ከተማ በአርኪቴክቸር ሳይሆን ሲሚንቶና አሸዋ ሳይጎበኛቸው በባሕላዊ የምህንድስና ጥበብ የተሠሩ



ውብና ማራኪ ጥንታዊ አረንጓዴ መንደሮች በሁሉም የጉራጌ ወረዳዎች ውስጥ እንደሚገኙ ይጠቁማሉ።

እያንዳንዱ ጀፎረ መቼ እንደተመሰረተ በውል ባይታወቅም ከመኖሪያ መንደሮቹ ጋር አብሮ እንደተመሰረተ ግን ይነገራል ይላሉ፡፡ ጀፎረ በየቅጥር ግቢዎቹ ውስጥ ሶስት አይነት (ጉየ፣ ሐራር እና ዘገር የሚባሉ) የሳር ክዳን ቤቶች ተመሳጥረው በረድፍ በሚታዩባቸው ሰፈሮች መካከል ቀጥ ብሎ የሚያልፍ እንደሆነም ይጠቅሳሉ፡፡

ኮረብታ፣ ወንዝ፣ ሸለቆ፣ ገደላገደል፣ ጫካ፣ ወዘተ ቢያጋጥመው የማይቋረጥ ወደ ግራ ወይንም ወደ ቀኝ

የገጠር ኮሪደር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






አቶ አሸናፊ ሙሉጌታ

# በቱሪዝሙ ዘርፍ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሆቴሎች አገልግሎት አሰጣጥን ማሳደግ ይገባል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ በቱሪዝሙ ዘርፍ ያላትን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሆቴሎች አገልግሎት አሰጣጥን ማሳደግ እንደሚገባ የከተማዋ ሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያዎች ማህበር አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያዎች ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ አሸናፊ ሙሉጌታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አዲስ አበባ በቱሪዝሙ ዘርፍ ያላትን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በተለይም የሆቴል እና መሰል አገልግሎቶችን ማሳደግ ይገባል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ሆነ ከከተማዋ ውጭ የሚገኙ ሆቴሎች እና ሬስቶራንቶች የመሰረተ ልማት እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጥ በሚጠበቀው መጠን እያደገ አለመሆኑን ጠቅሰው፤ ማህበሩም ቀደም ብለው ሥራ ለጀመሩት የጎደላቸውን በመለየት ማሟላት የሚችሉበትን መንገድ የማሳወቅ እንዲሁም አዲስ ለሚሰማሩትም የማማከር ሥራ እየሠራ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

እንደ አቶ አሸናፊ ገለጻ፤ የአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ መስህቦች የሚገኙባት እና የበርካታ ቱሪስቶች መዳረሻ እንደመሆኗ በከተማዋ የሚገኙ ባህላዊና ዘመናዊ ሆቴልና ሬስቶራንቶች ከተማዋን የሚመጥን አገልግሎትና መሰረተ ልማት ማሟላት አለባቸው፡፡

በመሆኑም ከትላልቅ ሆቴሎች ባለፈ በአብዛኛው የውጭ ጎብኚዎችና የሀገር ውስጥ ነዋሪዎች አገልግሎት የሚያገኙባቸው መደበኛ ካፌና ሬስቶራንቶች ድረስ የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶችን ማሟላትና የአገልግሎት አሰጣጥ ማሳደግ ወሳኝ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በአብዛኛው በከተማው በሚገኙ ሆቴሎች የእሳት አደጋ መውጫ የማያሟሉና የደንብ ልብስ አለባበስ ሥርዓት የሌላቸው መሆኑን  አንስተው፤ ከመስተንግዶ ሠራተኞች የደንብ ልብስ አለባበስ ጀምሮ የሚጠቀሙት ቋንቋ እና መስተንግዶ ደረጃቸውን የጠበቁ መሆን አለባቸው ብለዋል፡፡

እንዲሁም የእሳት አደጋ መውጫ፣ የመጸዳጃ ቤቶች ጥራት፣ የመኝታ እና ምግብ መስተንግዶዎች ወጥ እና ዓለም አቀፍ መስፈርት የሚያሟሉ ማድረግ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

በመሆኑም በከተማው ብሎም በሀገር አቀፍ ደረጃ የሆቴሎች አገልግሎት አሰጣጥና መሰረተ ልማት በማሟላት ደረጃውን የጠበቀ መስተንግዶ በመስጠት የከተማዋን ገጽታ መገንባትና ጎብኚዎች የቆይታ ጊዜያቸውን እንዲያራዝሙ ያደርጋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡ ይህም ከሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ለኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ማህበሩ የሀገሪቱን የቱሪዝም ዘርፍ ወደትልቅ ደረጃ ለማድረስ ዓላማ ይዞ ከተቋቋመ አንድ ዓመት ከአምስት ወር ጊዜ ብቻ ቢሆነውም ብዙ ተግባራትን ያከናወነ መሆኑን ገልጸው፤ ከ500 በላይ አባላትን በማፍራት የባለሙያዎች ስልጠና፣ የሆቴልና ሬስቶራንቶች የገበያ ላይ ስልጠናና የማማከር ሥራ እየሠራ እንደሚገኝ አቶ አሸናፊ አስታውቀዋል፡፡

# የወጋገን ባንክ አጠቃላይ ሀብት 65 ነጥብ 7 ቢሊዮን ደረሰ

## - ባንኩ የሰጠው የብድር መጠን 45 ነጥብ 18 ቢሊዮን ብር ደርሷል

**ማርቆስ በላይ**




አዲስ አበባ፡- ወጋገን ባንክ አጠቃላይ ሀብቱ 65 ነጥብ 7 ቢሊዮን መድረሱን አስታወቀ፡፡ ባንኩ የሰጠው የብድር መጠን 45 ነጥብ 18 ቢሊዮን ብር መድረሱም ተመላክቷል።

የወጋገን ባንክ አክሲዮን ማህበር 31ኛ መደበኛና 15ኛ አስቸኳይ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በአዲስ አበባ ተካሂዷል፡፡

የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ  ሰብሳቢ አቶ አብዱሽ ሁሴን የባንኩን የ2023/24 ዓመታዊ ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት እንደገለጹት፤ ወጋገን ባንክ ከታክስ በፊት 2 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ትርፍ ያስመዘገበ ሲሆን ከታክስ በኋላ 1 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ትርፍ አስመዝግቧል።

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የባንኩ ተቀማጭ ገንዘብ 52 ነጥብ 12 ቢሊዮን ብር ደርሷል ያሉት ሰብሳቢው፤ የባንኩ ከወለድ ነጻ ተቀማጭ ገንዘብም 2 ነጥብ 47 ቢሊዮን ብር ደርሷል ብለዋል።

ባንኩ ለተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች የሰጠው የብድር መጠን 45 ነጥብ 18 ቢሊዮን ብር መድረሱን ጠቅሰው፤ 12 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ብድር መሰብሰብ መቻሉን ገልጸዋል።

በበጀት ዓመቱ 305 ሚሊዮን ዶላር የውጪ ምንዛሬ ማግኘት መቻሉን በመግለጽ፤ በአለፈው ዓመት ከተገኘው የውጪ ምንዛሬ መጠን 27 በመቶ እድገት እንዳለውም ተናግረዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የባንኩ አጠቃላይ ሀብት 65 ነጥብ 7 ቢሊዮን ደርሷል ያሉት ሰብሳቢው፤ የባንኩ አጠቃላይ ካፒታልም 9 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ደርሷል ብለዋል።

የባንኩ የተከፈለ ካፒታል አምስት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር መድረሱን ጠቅሰው፤ ባንኩ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊደርስበት ካቀደው 20 ቢሊዮን ብር የተከፈለ ካፒታል አንጻር ዝቅተኛ በመሆኑ የባንኩን ካፒታል ለማሻሻል እንደሚሰራ ገልጸዋል።

በዓመቱ ከልዩ ልዩ የገቢ ምንጮች 9 ነጥብ 8 ቢሊዮን አጠቃላይ ገቢ ማስመዝገብ መቻሉን በመግለጽ፤ ከአጠቃላይ የባንኩ ገቢ ውስጥ የወለድ ገቢ 69 በመቶ ድርሻ እንዳለው ጠቁመዋል።

ባንኩ በካፒታል ማሳደግ፣ ሀብት ማሰባሰብ፣ በውጪ ምንዛሬ ግኝት፣ በብድር አሰባሰብና በሌሎች መለኪያዎች አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ መቻሉን ጠቅሰው፤ በቀጣይ የደንበኞችን እርካታ የበለጠ በማሳደግ፣ ተደራሽነቱን በማስፋት፣ በቴክኖሎጂ የታገዘ ዘመናዊ አገልግሎቶችን በማስተዋወቅና ማህበራዊ ኃላፊነቱን በመወጣት  እንደሚሰራ ገልጸዋል።

# አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደቱ አሳታፊና ሃሳቦች ያለምንም ተጽእኖ የተንሸራሸሩበት ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**



ቦንጋ፡- በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የተካሄደው አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደት አሳታፊና ሃሳቦች ያለምንም ተጽእኖ የተንሸራሸሩበት እንደነበር የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አስታወቀ።

ኮሚሽኑ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ሲያካሂደው የነበረውን የአጀንዳ ማሰባሰብና ለሀገራዊ የምክክር ጉባዔ ተወካዮችን የማስመረጥ ሂደት አጠናቋል።

የምክክር መድረኩ ተወካዮች አጀንዳዎቻቸውን ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ምክትል ዋና ኮሚሽነር ሂሩት ገብረስላሴ፣ ኮሚሽነር ሙሉጌታ አጎ እና ዘገየ አስፋው በይፋ አስረክበዋል።

ምክትል ዋና ኮሚሽነር ሂሩት እንደገለጹት፤ ኮሚሽኑ በክልሉ ያካሄደው የምክክር ሂደት ውጤታማ ሆኖ ተጠናቋል፡፡ ክልላዊ ምክክሩና አጀንዳ የማሰባሰብ ሂደቱ አሳታፊ፣ አካታችና ሃሳቦች ያለምንም ገደብ እና ተጽእኖ ተንሸራሸረውበታል፡፡

በመጀመሪያው ምዕራፍ አንድ ሺህ የሚሆኑ ከ10 የተለያዩ ማህበራዊ መሠረቶች የተወከሉ ተወካዮች በሰፊው ተመካክረው አጀንዳዎቻቸውን ማሰባሰባቸውን ያነሱት ምክትል ዋና ኮሚሽነሯ፤ በሁለተኛው ምዕራፍም አንድ ሺህ 200 የሚሆኑ የክልሉ ባለድርሻ አካላትና የህብረተሰቡ ተወካዮች ሰፊ ምክክር ማድረጋቸውን ጠቁመዋል፡፡

እንደ ምክትል ዋና ኮሚሽነሯ ገለፃ፤ 11 ክልላዊና ሀገራዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በተለያየ ደረጃ ላይ ያሉ የክልሉ መንግሥት ተወካዮች፣ ተቋማትና ማህበራት፣ ታዋቂና ተቀባይነት ያላቸው ሰዎች በጥልቅ መክረውና አጀንዳዎችን አደራጅተው ለኮሚሽኑ አስረክበዋል፡፡

በክልሉ የምክክር ሂደት አጀንዳዎችን ከማሰባሰቡ ባሻገር ጊዜ ወስዶ፣ ተከባብሮና ተደማምጦ የጋራ አጀንዳዎችን መቅረጽ እንደሚቻል በተግባር የታየበት ነበር ያሉት ኮሚሽነሯ፤ እንዲሁም ለሀገራዊ ምክክር ጉባዔው ተሳታፊ የሚሆኑ ተወካዮች ውክልናም ግልጽና ዴሞክራሲያዊ በሆነ ሁኔታ መከናወኑን አንስተዋል።

ኮሚሽኑ እንደ ሀገር ላሉብን የሃሳብ ልዩነቶችና አለመግባባቶች መንስኤ የሆኑ አጀንዳዎችን በመቅረጽ መግባባት ላይ  እንዲደርስ እየሰራ ነውም ብለዋል።

እንዲሁም ሌሎች አጀንዳዎች በየደረጃው ላሉ የሚመለከታቸው አካላት እንዲቀርቡና መፍትሄ እንዲያገኙ እንደሚሰራ የገለጹት ምክትል ዋና ኮሚሽነሯ፤ ቀጣዩ ተግባር የሚሆነው ሀገራዊ የምክክር ጉባዔውን ማካሄድ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ይህ ታሪካዊ ዕድል ለሀገሪቱ ቀጣይ ዕጣ ፈንታ መልካም መሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን በመረዳት፤ በሂደቱ እየተሳተፉና ተገቢውን ድጋፍ እያደረጉ ላሉ አካላት ኮሚሽኑ እንደሚያመሰግን ተናግረዋል።

በአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረኩ ላይ በከፍተኛ ሀገራዊ ስሜት ለተሳተፉ ሁሉም የህብረተሰብ ተወካዮች እና ልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ለመድረኩ ስኬት ለተጉ አካላት ኮሚሽኑ ምስጋና ያቀርባል ብለዋል።

በቀጣይም የተሳታፊዎች ልየታና አጀንዳ የማሰባሰብ የምክክር መድረክ ባልተካሄደባቸው አካባቢዎች እንደሚካሄድ ምክትል ዋና ኮሚሽነሯ አመላክተዋል።

በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች፣ በሲዳማ፣ በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በሐረር፣ በአፋር፣ በሱማሌ፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች አጀንዳ የማሰባሰብ ሥራውን በተሳካ ሁኔታ ማከናወን መቻሉን ኮሚሽኑ መግለፁ የሚታወስ ነው።

# የሀዋሳ የኮሪደር ልማት ለቱሪዝም ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ነው

**ማህሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ፡- በሀዋሳ ከተማ እየተገነባ የሚገኘው የኮሪደር ልማት ለከተማው የቱሪዝም እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር መሆኑን የሲዳማ ክልል የመንገድ ልማትና ትራንስፖርት ቢሮ አስታወቀ፡፡ በከተማው ስድስት ነጥብ ሰባት ኪሎ ሜትር የኮሪደር ልማት እየተሠራ ነው።

በሲዳማ ክልል የመንገድ ልማትና ትራንስፖርት ቢሮ የኮሙኒኬሽን ኃላፊ አቶ ደስታ ዳንጮ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሲዳማ ክልል መቀመጫ በሆነችው ሀዋሳ ከተማ እየተገነባ የሚገኘው ስድስት ነጥብ ሰባት ኪሎ ሜትር የኮሪደር ልማት ለከተማው የቱሪዝም እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

በከተማው በመጀመሪያ ዙር የኮሪደር ልማት ሥራ በተመረጡ አካባቢዎች ላይ የተለያዩ ተግባራትን ያካተተ ሥራ እየተካሄደ መሆኑን አንስተው፤ ከዚህም መምቦ ሆቴል እስከ ሪፈራል ሆስፒታል አደባባይ አንድ ነጥብ አንድ ኪሎ ሜትር የሚሸፍነው ሥራ ከ90 በመቶ በላይ ግንባታው ተጠናቅቋል ብለዋል፡፡

ከሻፌታ አደባባይ እስከ ሳውዝ ስፕሪንግ እንዲሁም ከመሀል መገንጠያ እስከ ፍቅር ሀይቅ እና ከታቦር መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እስከ ግሎባል ጋራጅ በአጠቃላይ አምስት ነጥብ ስድስት ኪሎ ሜትር የሚሆን መንገድ የሰነድ፣ ዲዛይን ዝግጅት እና ካሳ ክፍያ የመሳሰሉት ቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተጠናቅቀው ለግንባታ ዝግጁ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

በቀጣይም ወጣ ያለ አጥር እና መንገድ ዳር ቤቶች የማፍረስ እንዲሁም መንገዶችን በማስፋት ወደግንባታ የሚገባ መሆኑን አቶ ደስታ ገልጸዋል፡፡

የኮሪደር ልማቱ ምቹ የእግረኛ መንገድ፣ ጭስ አልባ ትራንስፖርት ለማስፋፋት የሚያግዝ የብስክሌት መንገድ፣ የአረንጓዴ ልማት፣ ፋውንቴን፣ መዝናኛ፣ የልጆች መጫወቻ እና የስፖርት ማዘውተሪያዎችን የሚያካትት መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

በተጨማሪም በከተማው የመንገድ ማስፋፊያ ሥራዎች እየተሠራ ሲሆን፤ ከ30 እስከ 50 ሜትር ስፋት ያላቸው እና በአጠቃላይ 35 ኪሎ ሜትር የሚሸፍኑ 10 መንገዶች ጥናት አልቆ ውሳኔ እየተጠበቀ መሆኑን ተናግረዋል፡፡


አቶ ደስታ እንደገለጹት፤ ከተማዋ የቱሪስት ማዕከል ከመሆኗ አንጻር ለመዝናናት እና ለኑሮ ተስማሚ ከሚባሉ ከተሞች ተጠቃሽ ናት፡፡ የኮሪደር ልማቱ የከተማዋን ገጽታ ከሚጠበቀው በላይ ከፍ የሚያደርግና ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ነው፡፡

እንዲሁም ከተማዋ ያላትን የቱሪዝም መስህብነትና ተመራጭነት በማሳደግ ለከተማው ብሎም ለክልሉ የቱሪዝም እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

## በኢትዮጵያ 90 ሆስፒታሎች የቫይራል ጉበት በሽታ ምርመራና ህክምና እየሰጡ ነው

### - የበሽታው የሥርጭት ምጣኔ ከኤች.አይ.ቪ በዘጠኝ እጥፍ ብልጫ አለው

**ማርቆስ በላይ**




አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ የቫይራል ጉበት በሽታ ምርመራና ህክምና በ90 ሆስፒታሎች ላይ እየተሰጠ መሆኑን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ የቫይራል ጉበት በሽታ የሥርጭት ምጣኔ ከኤች.አይ.ቪ በዘጠኝ እጥፍ ብልጫ እንዳለውም ተገልጿል፡፡

በጤና ሚኒስቴር የኤች.አይ.ቪ፣ የቫይራል ሄፒታይተስና የአባላዘር በሽታ መከላከልና መቆጣጠር መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፍቃዱ ያደታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የቫይራል ጉበት በሽታ ምርመራና ህክምና በ90 ሆስፒታሎች እንዲሰጥ እየተደረገ ነው፡፡

የቫይራል ጉበት በሽታ የማህበረሰብ ጤና ችግር እየሆነ መጥቷል ያሉት አቶ ፍቃዱ፤ በሀገሪቱ የበሽታው ምርመራና ህክምና በ90 ሆስፒታሎች እንዲሰጥ እየተደረገ ነው ብለዋል።

በበሽታው ቁጥጥር ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ድጋፍ እንደሌለው ጠቅሰው፤ በመንግሥት በጀት የተወሰኑ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

በሆስፒታሎቹ የሚካሄደው ምርመራና ህክምና ከሀገሪቱ ሕዝብ ቁጥር አንጻር በቂ አይደለም ያሉት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ ምርመራውንና ህክምናውን ለማስፋፋት መድኃኒቶችንና መመርመሪያዎችን በመግዛት ተደራሽ እየተደረጉ ይገኛል ብለዋል፡፡

የጉበት በሽታ ከፍተኛ የሆነ የሥርጭት ምጣኔ ያለው ሲሆን፤ ዘጠኝ በመቶ ሥርጭት እንዳለው ጠቅሰው፤ ይህም ከኤች.አይ.ቪ የሥርጭት ምጣኔ በዘጠኝ እጥፍ ብልጫ ያለው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በቫይረሱ ላይ የግንዛቤ ሥራዎችን መስራት እንደሚያስፈልግ በመግለጽ፤ በተለይም የባህሪ ለውጥ ተግባቦቶች ላይ በትኩረት መስራት እንደሚጠይቅ ተናግረዋል፡፡

የቫይራል ጉበት በሽታ ኤ፣ቢ፣ሲ፣ዲ እና ኢ ተብለው የሚታወቁ አምስት አይነት ስያሜዎች አሉት ያሉት አቶ ፍቃዱ፤ ቢ የቫይራል ጉበት በሽታ በመባል የሚታወቀው ከእናት ወደ ልጅም የሚተላለፍ በመሆኑ ማናቸውም ነፍሰጡር እናቶች ከወሊድ በፊት ምርመራ ማድረግ አለባቸው ብለዋል፡፡

የቫይራል ጉበት በሽታ ላይ ምርመራና ህክምና እየተሰጠ ቢሆንም ተደራሽነቱ ውስን መሆኑን ጠቅሰው፤ በሽታውን በተመለከተ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ጥናቶች እየተካሄዱ እንደሚገኝም ጠቁመዋል፡፡

በአጠቃላይ የጉበት በሽታ ሥርጭት እየሰፋ በመሆኑ ህብረተሰቡ ራሱን መጠበቅ እንዳለበት በመግለጽ፤ መንግሥት ከመቼውም ጊዜ በላይ በሄፓታይተስ ላይ በትኩረት እየሰራ እንደሚገኝም ተናግረዋል፡፡

## በክልሉ የወባ ወረርሽኝን ለመከላከል የአጎበር ሥርጭትና የኬሚካል ርጭት ተካሄደ

**ሔርሞን ፍቃዱ**



አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል የወባ ወረርሽኝን ለመከላከል የአጎበር ሥርጭትና የኬሚካል ርጭት መካሄዱን የክልሉ ጤና ቢሮ አስታወቀ፡፡

በቢሮው የበሽታ መከላከልና መቆጣጠር ባለሙያ አቶ ገብረመድህን ክንፉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ በትግራይ ክልል በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ 93 ሺህ ሰዎች በወባ በሽታ ተይዘዋል፡፡ በበሽታው ምክንያት ዘጠኝ ሰዎች ህይወታቸው ማለፉም ተገልጿል፡፡

በሽታው ከተወሰነ ደጋማ አካባቢዎች ውጭ እንደ ወረርሽኝ ተከስቷል ያሉት አቶ ገብረመድህን፤ ወቅቱ ለትንኝ መራባት ምቹ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የአካባቢ ንፅህና አለመጠበቅ በሽታው በዋነኝነት እንዲበዛ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል ተጠቃሽ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የበሽታው ስርጭት በተያዘው ሩብ ዓመት በመጨመሩ የባለ ድርሻ አካላት እገዛ አስፈላጊ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም እስከ አሁን በሽታውን ለመከላከል ከአንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን በላይ የወባ መከላከያ አንጎበር ለሰላሳ ስድስት ወረዳዎች መከፋፈሉን ጠቅሰው፤ በተጨማሪም ከ300 ሊትር በላይ የሚረጭ የወባ ትንኝ መከላከያ ኬሚካል ለሃያ ስድስት ወረዳዎች መከፋፈሉን አመልክተዋል፡፡

ይህ የመከላከል ሥራ ቀጣይነት እንዲኖረው እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤የመድኃኒት አቅርቦት እና የባለሙያ እጥረትም በሽታውን ለመቆጣጠር አዳጋች እንዳደረገው አስረድተዋል።

በዋናነት ወቅቱ የፈጠረው ምቹ የትንኝ መራባት ሁኔታ በቁጥጥር በማዋል፤እንዲሁም የበሽታው ምልክት ሲታይ በፍጥነት ወደ ህክምና ሄዶ በመታከም መከላከል እንደሚቻል አብራርተዋል፡፡

እየተሠራ ያለው የመከላከል ሥራ በቂ አለመሆኑን የገለጹት ኃላፊው፤ በተለይ ህብረተሰቡ በተቻለው መጠን አስፈላጊውን የጥንቃቄ ሥራ መሥራት እንዳለበት አሳስበዋል።

ማኅበረሰቡ አካባቢው ላይ ያሉ ውሃ ያቆሩ ቦታዎች በመድፈን፣ አካባቢን በማፅዳት እንዲሁም ሲተኙ አንጎበር በአግባቡ በመጠቀም በበሽታው የመያዝ ዕድልን መቀነስ እንደሚችሉ አመልክተዋል፡፡

# የግል አልሚዎች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች የሚፈታ አሠራር ተዘርግቷል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ ፦ መንግሥት ለግል አልሚዎች ትኩረት ሰጥቶ ችግሮችን የሚፈታበት አሰራር ዘርግቶ እየሰራ መሆኑን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ።

የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ሴክሬታሪያት 15ኛው የንግድ ሚኒስትሮች ካውንስል ጉባኤ ተሳታፊዎችና የአባል ሀገራት የንግድ ሚኒስትሮች የወጪ ንግድ ምርቶች ማሳያ ማእከልንና ገላን የሚገኘው ኤ.ኤም.ጂ ኢንዱስትሪያል ፋብሪካ ጐብኝተዋል።

በጉብኝቱ ወቅት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ ኢትዮጵያን ለግል አልሚዎች ምቹ የማድረግ ስራ እየተሰራ ነው።

የግል አልሚዎች ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማስቻል መንግሥት ብዙ እየሰራ ነው ብለዋል።

የግል አልሚዎች ለሀገር እድገት የጀርባ አጥንት ናቸው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ዕድገት እየጨመረ ሲመጣ ሀገር በቀል አልሚዎች ያስፈልጋሉ። በመሆኑም መንግሥት ለግል አልሚዎች ትኩረት ሰጥቶ ችግሮችን የሚፈታበት አሰራር ዘርግቶ እየሰራ ይገኛል ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፣ በኢትዮጵያ እድገት ውስጥ የግል አልሚዎች ሚና አይተኬ በመሆኑ በፖሊሲና ስትራቴጂ የመደገፍ ሰፊ ርብርብ እየተደረገ ነው። የመንግሥት ድጋፍ ባይኖር ኤ.ኤም .ጂን ጨምሮ በርካታ የግል ድርጅቶች ለውጤት አይበቁም ነበር። መንግሥት አቅሙ በፈቀደው ልክ ሁሉንም አልሚዎች የመደገፍ የማበረታታት ስራ እየሰራ ነው።

ከሀገር ውስጥ ወጥተው አህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ ውድድርን እንዲወዳደሩ የማድረግ ጥረት መኖሩን ጠቅሰዋል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሊያድግ የሚችለው በኢትዮጵያዊያኖች ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ከውጭ ሲታይ ብዙ የአፍሪካ ሀገራት ንግድና ኢንቨስትመንት ያለ ይመስላል፣ ነገር ግን ብዙ ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች የተያዙት በውጭ ዜጎች ነው። የኢትዮጵያ ሀብት 99 በመቶ የተያዘው በኢትዮጵያ ነው ብለዋል።

አፍሪካ አህጉራዊ ነፃ ንግድ ቀጣና አንዱ እቅዱ የግል አልሚዎች ለኢኮኖሚው አጋዥ እንዲሆኑ ማድረግ ነው ያሉት ዶክተር ካሳሁን፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ውስጥ ባለሀብቶች በስፋት እንዲሳተፉ ታደርጋለች ሲሉ ገልጸዋል። እንዲሁም የዓለም የንግድ ድርጅትን ለመቀላቀል ሰፊ ስራ እየተሰራ መሆኑን አንስተው፤ ይህም ለግል አልሚዎች ትልቅ የገበያ እድልን ይፈጥራል ሲሉ አስረድተዋል።

የዓለም ንግድን የምንቀላቀለው የግሉን ዘርፍ ይዘን ነው፣ የግሉ ዘርፍ አምራች፣ ተወዳዳሪና ብቁ እንዲሆን ከማድረግ ረገድ መንግሥት የበኩሉን ሚና እየተወጣ ነው ያለው። ይበልጥ አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል ሚኒስትሩ።

እንደ ካሳሁን (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ሴክሬታሪያት 15ኛው የንግድ ሚኒስትሮች ስብሰባ በአዲስ አበባ እንዲካሄድ መወሰኑ ትልቅ እድል ነው። በኢትዮጵያ መልካም ገጽታና የተሰሩ ስራዎች ለማስጐብኘት እድል የሰጠ ነው። ከሰሞኑን አዲስ አበባ በብዙ የውጭ ዜጐች የተጎበኘችበት ነው።

የተጠናቀቀው የአፍሪካ 15ኛው የንግድ ሚኒስትሮች መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የቀረቡ ውሳኔዎችን አጽድቋል።

## “ቤኑና መንደር አስቸጋሪ…

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

መንደሩ ከመዝናኛ ስፍራዎች በተጨማሪ የፍራፍሬ ልማትና የሌማት ትሩፋትን ማካተቱ ደግሞ ግብርናን ከቱሪዝም መዳረሻ ጋር ለማስተሳሰር ትምህርት የሚወሰድበት ስለመሆኑ ገልጸዋል።

በመንደሩ የብርቱካን፣ የሎሚ፣ የፓፓዬና የማንጎ ልማት እንዲሁም ዶሮ፣ ግመል፣ ከብትና ፍየል የማርባት ስራ እየተከናወነ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

የቤኑና መንደር ግንባታም በኢትዮጵያ መንግሥት፣ የግሉ ዘርፍ እና የተባበሩት አረብ ኢምሬትስ መንግሥት ትብብር የተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።

የስካይ ላይት ሆቴል መንደሩን ተረክቦ የማስተዳደር ሥራ እንደሚያከናውንም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጨምረው አስታውቀዋል ሲል ኢዜአ ዘግቧል።

# የገጠር ኮሪደር…

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ታጥፎ እንደገና ስሙንና መልኩን ይዞ የሚቀጥል መሆኑንም በጽሑፋቸው ያነሳሉ። ከአንድ መንደር ተነስቶ ወደሌሎች መንደሮች የሚዘልቅ፣ ወረዳን ከወረዳ የሚያገናኝ፣ ሄዶ ሄዶ የማይደክመው፣ ርዝመቱ ከየት ተነስቶ የት እንደሚደርስ የማይታወቅ ነው ይላሉ፡፡

ወንዝ ካጋጠመው፣ ተራራ ከተጋረጠበት፣ ሸለቆ እንቅፋት ከሆነበት እነዚህን ሁሉ በጎን አልፎ በጀመረው ዓይነት የሚዘልቅ፣ ሙሉውን ለምለም ሳር የለበሰ፣ ደልዳላ፣ በየመካከሉ የዝግባ፣ የዋርካ፣ የሾላ፣ የሃበሻ ጽድ የመሳሰሉ ዕድሜ ጠገብ ዛፎች የሚታዩበት ሰፊ የገጠር አውራ ጎዳና ነው፡፡

ባለሙያው እንደሚሉት፤ ጀፎረ በጣም ፅዱና ለአይን የሚማርክ ነው፡፡ በጥንት ጊዜ የጎን ስፋቱ ከ12 ዘንግ በላይ እንደነበር ይነገራልም። በአንዳንድ ሰፈሮች ውስጥ ስፋቱ በተለያዩ ምክንያቶች እየጠበበ ቢመጣም በአሁኑ ጊዜም ቢሆን ከ40 እስከ 50 ሜትር ያህል የጎን ስፋት ያላቸው ጀፎረዎች በተለያዩ መንደሮች ውስጥ መኖራቸውን በጽሑፋቸው ያብራራሉ።

በተጨማሪም ጀፎረ የአንድ ሰፈር፣ ጎሳ፣ መለያ ብቻ ሳይሆን እንደማናቸውም ቅርሶቻችን የሀገራችን አኩሪ ቅርስ እንደመሆኑ ይህንን በልዩነት የሚታየውን ቅርሳችንን ተገቢውን እውቅና እንዲያገኝ ለማድረግ እንደ ሀገርም ትርጉም ያለው ጥረት ሊደረግ ይገባል ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

የጉራጌ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ ወይዘሮ መሰረት አመርጋ በበኩላቸው፤ ጀፎረ በሀገር በቀል እውቀትና ጥበብ ስፋቱ ተለክቶ የተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ ርዝመቱ ግን ተወስኖ የማይቀመጥ መሆኑን ያስረዳሉ።

የገጠር ኮሪደር ተምሳሌት የሆነው ጀፎረ በርካታ ፋይዳዎች እንዳሉት የሚገልጹት ኃላፊዋ፤ ባህላዊ ዳኝነት፣ የእናቶች ቀን፣ የልጃገረዶች ቀን፣ የተለያዩ በዓላት፣ የፈረስ ጉግስ፣ የደመራ ሥነሥርዓት እንዲሁም ሌሎች በርካታ ኩነቶች እንደሚካሄዱበት ነው ያስታወቁት፡፡

የአካባቢው ማህበረሰብ እንደዝግባ፣ ጽድና ሌሎችም ሀገር በቀል የሆኑ ዛፎችን እንደጥላ ለመጠቀምና ለማስዋብ የሚሆኑ ነገሮችን ይተክላል። ከዚህ ባሻገር ግን ማንኛውም ሰው የኔ ነው በሚል አጥሩን ገፋ አድርጎ ቢያጥር፣ የጀፎረ መንገዱን ቢያጠብ፣ የተለያዩ ችግኝና ሰብሎችን አምርቶ ቢጠቀም፣ ባልተገባ መንገድ ቢቆፍር በማህበረሰቡ የዳኝነት ሥርዓት መሰረት ተጠያቂ እንደሚሆን ይጠቅሳሉ፡፡

ከወልቂጤ ወደ ቡታጅራ የሚወስድ ወደ 80 ኪሎ ሜትር የሚሆን አስፓልት ሲሰራ አንድም ቤትና ቋሚ ንብረት እንዳልተነሳና ካሳ እንዳልተከፈለ ያስታወሱት ኃላፊዋ፤ ማህበረሰቡ ቀድሞ ገብቶት የቀየሰው የጀፎረ መንገድ በመኖሩ አስፓልቱ እንደተገነባና ከመንገዱ ዳር ለእግረኛ እና ለእንስሳት የሚሆን መሬት ጭምር እንዳለም ጭምር ይጠቁማሉ።

በክረምት ጊዜ ባለሀብቶች መኪና ይዞ ለመግባት ሲሉ ጀፎረውን ጠጠር የማልበስና የነበረውን ገፅታ የመቀየር፣ አጥሩን በቆርቆሮና በብሎኬት የማጠር የመሳሰሉት ነገሮች ግን ቀሪ ሥራዎችን የሚጠይቁ መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡

የገጠር ኮሪደር ምሳሌ የሆነውን ጀፎረ ማስፋፋትና መጠበቅ እንደሚገባም አንስተው፤ የገጠር ኮሪደር ልማቱ ፅዱ አካባቢን መፍጠር፣ በኢኮኖሚ የተሻለ የአኗኗር ዘይቤን መከተል፣ አጥሩ በቆርቆሮ ሳይሆን በቀርከሀ የሆነ፣ ከቤቱ ጓሮ የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬ የሚተክልና የእንስሳት ተዋፅኦ እና የዶሮ እርባታን አቀናጅቶ የያዘ መሆኑን አስታውሰዋል።

አልፎ አልፎ ካልሆነ በቀር አብዛኛውን ጊዜ በዞኑ ከብቶችና ሰዎች በአንድ ቤት እንደማያድሩም ጠቅሰዋል፡፡

እንደባህል ቱሪዝም ቢሮ መሰረተ ልማቶች ጀፎረውን በማያበላሽ መልኩ የልማት ስራዎች እንዲከናወኑ የማድረግ ስራዎችን ማጠናከር እንዳለባቸው ነው ያወሱት።

የቱሪዝም አቅም መሆን የሚችል ከመሆኑ አኳያም የቱሪስት መዳረሻ ተሰርቶለት ቢጎበኝ ተጨማሪ ገቢ መፍጠር እንደሚያስችል ይገልጻሉ።

ጀፎረ በዓለም አቀፍ ደረጃም እንደቅርስ እንዲመዘገብ ጥያቄ ቀርቦ ምላሽ እየተጠበቀ መሆኑን ጠቁመው፤ የገጠር ኮሪደሩን በተለያዩ አካባቢዎች በማስፋፋት ምቹና ለኑሩ ተስማሚ የሆነ አካባቢን መፍጠር እንደሚገባም ያስረዳሉ።

በተጨማሪ የገጠር ቤቶች እንደከተማ በፕላን ካለመሰራታቸው አኳያ በዞኑ የሚታየው በምህንድስና የተሰራ የሚመስል ዲዛይን ጥልቅ ጥናትና ምርምር ይፈልጋል ይላሉ፡፡



# ድህረ ምርት ብክነት-…

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ምርቱ የሚባክነው ድህረ ምርት ስብሰባ መሆኑን ጠቅሶ፤ ምርት በመሰብሰብ፣ በማድረቅ እና በማከማቸት ላይ መሆኑን ነው ያሚያስረዳው። እነዚህ ኪሳራዎች በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አላቸው።

በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የአግሮ ኢኮኖሚስት መምህር አሰፋ ጥላሁን (ዶ/ር)፤ የሕዝብ ቁጥር እያደገ በመምጣቱ የምግብ ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱን ያነሳሉ፡፡ ከዚህ አኳያ የምርት ብክነት በቂ የምግብ አቅርቦትን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት ያበላሻል ይላሉ።

የምርት ብክነት የምግብ አቅርቦትን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት ከመጉዳቱም ባሻገር በአርሶ አደሩና በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ያስከትላል ይላሉ።

የዘመናዊ መሠረተ ልማት እጦት በተለይ በገጠር አካባቢዎች ዘመናዊ የማከማቻ ቦታ አለመኖሩ የድህረ ምርት ብክነት አንዱ መንስዔ ነው ያሉት አሰፋ (ዶ/ር)፤ ይህም ምርት ለብልሽት እና ለተባዮች ተጋላጭ እንዲሆን ያደርጋል ነው ያሉት።

ምርትን በባህላዊ መንገድ መሰብሰብ ለጉዳትና ለምርት መጥፋት ይዳርጋል። ደረጃውን ያልጠበቀ ግብአትም የሰብል ምርትንና ጥራትን ይቀንሳል ያሉት አሰፋ ጥላሁን(ዶ/ር)፤ በሀገሪቱ የሚስተዋለው የሰላም እጦት ሌላኛው የምርት ብክነት ምክንያት መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ድርቅና ጎርፍ ያሉ አስከፊ የአየር ሁኔታ ክስተቶች የግብርና ምርትን ሊያውኩ እና የድህረ ምርትን ብክነት ሊያባብሱ ይችላሉ ሲሉም ያነሳሉ። ስለዚህ የምርት ብክነትን ለመቀነስ የኢትዮጵያ መንግሥት እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ መተባበር አለባቸው ሲሉም ጠቁመዋል።

ዘመናዊ የምርት ማከማቻን መገንባት እና የትራንስፖርት አውታሮችን ማሻሻል ከምርት በኋላ የሚደርሰውን ኪሳራ ለመቀነስ ያስችላል። አርሶ አደሮችን በእውቀትና በክህሎት ማብቃት አሠራራቸውን በማሻሻል የምርት ብክነትን መቀነስ ይቻላል ነው ያሉት።

ጠንካራ የእሴት ሰንሰለቶች መዘርጋት ገበሬዎች ለምርታቸው ተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ማድረግ በድህረ ምርት የሚደርሰውን ኪሳራ እንዲቀንስ ያደርጋል ብለዋል።

ቆራጥ እርምጃ በመውሰድ ኢትዮጵያ ከምርት በኋላ የሚደርሰውን ኪሳራ በእጅጉ በመቀነስ የሕዝቦቿን የምግብ ዋስትና ማሻሻል ትችላለች የሚሉት ዶክተር አሰፋ፤ ይህ ደግሞ ከመንግሥት፣ ከግሉ ዘርፍ እና ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የተቀናጀ ጥረት እንደሚጠይቅ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ የድህረ ምርት ባለሙያዎች ማህበር ምክትል ፕሬዚዳንት ሙሉጌታ ተዓምር (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የመንግሥት ዋና ትኩረት የግብርና ምርቶችን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ላይ መሆኑን ያነሳሉ። ነገር ግን ከቅድመ ምርት አሠራሮች ጋር ሲነፃፀር ለድህረ ምርት አስተዳደር የተሰጠው ትኩረት አናሳ ነው ይላሉ።

ለድህረ ምርት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና መመሪያዎች ቴክኒካል ተስማሚነትን፣ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነትን፣ ማህበራዊ ተቀባይነትን እና የአካባቢን ዘላቂነት ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው ያሉት ሙሉጌታ (ዶ/ር)፤ በክልል የተመረቱ የተለያዩ የግብርና ምርቶች ከአንዱ ክልል ወደ ሌላ ክልል ወይም ክልሎች አካባቢዎች ወደ መዲናዋ እስኪደርሱ ድረስ እስከ 50 በመቶ እንደሚባከኑ ይገልጻሉ።

በእህል ምርቶች እስከ 30 በመቶ፤ በአትክልት እና በፍራፍሬ ምርቶች ደግሞ እስከ 50 በመቶ ድረስ የምርት ብክነት ይፈጠራል ያሉት ሙሉጌታ (ዶ/ር)፤ እየባከነ የሚገኘው የግብርና ምርትም በርካታ ኢትዮጵያን መመገብ የሚችል መሆኑን ይናገራሉ።

ለዚህ ደግሞ የግብርና ምርቶችን ለመሰብሰብ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን አለመጠቀም፣ የሎጅስቲክስ ችግር እና በሀገሪቱ የሚስተዋለው የሰላም እጦት ዋና ምክንያቶች ናቸው ነው ያሉት።

የምርት ብክነት ለምግብ ዋስትናው ከፍተኛ ስጋት መሆኑን በመጥቀስ፤ መንግሥት በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ላይ ኢንቨስት በማድረግ፣ ዘላቂ አሠራሮችን ማስተዋወቅ እንደሚኖርበት ያስገነዝባሉ፡፡

የእሴት ሰንሰለቶችን በማጠናከር የግብርና ዘርፉን ተግዳሮቶች መፍታት ላይ መንግሥት ማተኮር እንደሚኖርበት ጠቁመው፤ በዚህም የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እንደሚቻል ይገልጻሉ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኮንፈረንሶቹ የክልሉን ሕዝብ ከሰላም እጦት መታደግ የሚያስችሉ ስትራቴጂክ አቅሞች ናቸው!

በተለያዩ ጊዜያት እንደ ሀገር ያጋጠመን የሰላም እጦት በታሪካችን ባልተለመደ መልኩ ብዙ ዋጋ እንድንከፍል አስገድዶናል። የሀገርን ሕልውና አደጋ ውስጥ በመክተት ተመልሰን የግጭት አዙሪት ውስጥ እንድንገባ አድርጎናል። ለታሪካዊ ጠላቶቻችን እና ለኛ በጎ ለማይመኙ የውጪ ኃይሎች እንደ መልካም አጋጣሚ ሆኖ ፈትኖናል።

በዜጎች የበዛ የሕይወት መስዋእትነት፤ መላውን ሕዝብ ከዳር አስከዳር በብዙ ተስፋ ያነሳሳውን ለውጥ እና ለውጡ የተገዛበትን አስተሳሰብ ገና ከጅምሩ ለማምከን በውስጥ እና በውጪ ኃይሎች የተቀናጀ ርብርብ የተጀመረው ሀገር እና ሕዝብን ሰላም የመንሳት እንቅስቃሴ ዛሬም መላውን ሕዝባችንን እየፈተነው ይገኛል።

በኃይል ላይ የተመሰረተው፤ በዘመናት አንደ ሀገር የከፋ ዋጋ ሲያስከፍለን የቆየው አሮጌው የፖለቲካ ባህላችን፤ ባህሉ በፈጠረው አስተሳሰብ የተገሩት የፖለቲካ ልሂቃኖቻችን፤ ዛሬም ኃይልን የስልጣን ምንጭ አድርገው ማየታቸው፤ በዚህም ልባቸው መደንደኑ ለችግሩ መፈጠር መሰረታዊ ምክንያት ሆኗል።

ይህንኑ አሮጌ አስተሳሰብ እምቢ የሚል የማኅበረሰብ ንቃተ ህሊና መፍጠር አለመቻላችን፤ እነዚህ የፖለቲካ ልሂቃን ባልተገባ መንገድ ሀገርን መልሰው ወደ ግጭት አዙሪት መክተት እንዲችሉ መልካም አጋጣሚ ፈጥሯላቸዋል። ሀገር እና ሕዝብ ጊዜ ባለፈበት አስተሳሰባቸው ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍሉ አድርጓቸዋል።

ሕዝብን በሕዝብ ላይ፤ ሕዝብን በመንግስት ላይ የሚያነሳሱ የተዛቡ ትርክቶችን በመፍጠር፤ ለውጡን የራሱ አድርጎ በብዙ ተስፋ የተነቃቃው ሕዝባችን፤ ከለውጥ ተስፋው ለማለያየት ብዙ ለፍተዋል። የሀገርን ሕልውና አደጋ ውስጥ በከተተ መንገድ ስልጣንን በኃይል፣ በሁከትን እና በግርግር ለመያዝ ረጅም ርቀት ተጉዘዋል።

በዚህም በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን ለሞት እና ለአካል ጉድለት፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩትን ከቤት ንብረታቸው እንዲፈናቀሉ፤ ከፍተኛ መጠን ያለው የሀገር ሀብት ለውድመት ተዳርጓል። ጦርነት እና ግጭቶች በፈጠሩት ጫና ብዛት ያላቸው ዜጎች ለተለያዩ የስነልቦና ችግሮች ተጋልጠዋል።

ችግሩ ዛሬም በአማራ ክልል፤ የክልሉን ነዋሪዎች የለት ተዕለት ሕይወት ከመፈታተን አልፎ ሀገር በሚረከቡ ትውልዶች ላይ ሁለንተናዊ ጥፋት እያስከተለ ነው። በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ጽንፈኛ ኃይሎች ክልሉን የግጭት ማዕከል በማድረግ በብዙ ልፋት እና ሀብት የተገነቡ መሰረተ ልማቶች እንዲወድሙ አድርገዋል።

አጠቃላይ የሆነውን የክልሉን ነዋሪ ሕይወት ችግር ውስጥ በመክተት፤ በሰላም ወጥቶ የሚገባበትን፤ ማኅበራዊ መስተጋብሮቹን በሰላም የሚከውንበትን ዕድል አሳጥቶታል፤ ለሞት፣ለስደት፣ ለእገታ እና ለከፋ ማህበራዊ ምስቅልቅሎሽ ዳርገውታል። ቋንቋውን በሚናገሩ፣ ከማኅበረሰበዊ ማንነታቸው በተጣሉ በእነዚህ የጥፋት ኃይሎች /የገዛ ልጆቹ በታሪክ ሆኖ በማያውቅ መልኩ ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍል ሆኗል።

የክልሉን ሕዝብ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ነጻነት እንዲያጣ በማድረግ፣ ነገዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ዛሬዎቹም ትርጉም አልባ እንዲሆኑ፤ ትናንቶችን ናፋቂ በማድረግ፤ የለውጡ ዋዜማ ተስፋው እና ሕልሙ እንዲደበዝዝ አድርገዋል።

ሀገር ተረካቢ የሆነው ትውልድ ሀገር የሚረከብበትን አቅም እንዳይገነባ ትምህርት ቤቶችን ከመዝጋት ጀምሮ፤ የመማር ማስተማሩን ሂደት በመቃወም ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው እንዳይገኙ አድርገዋል፤ መምህራንን በአደባባይ በመግደል በትውልዱ ላይ ያላቸውን የጥፋት ተልዕኮ በተጨባጭ አሳይተዋል።

መንግስት በየወቅቱ የሚያቀርበውን የሰላም ጥሪ እንደ አቅመቢስነት በማየት፤ በተዛቡ ትርክቶች እና መሰረት አልባ ፕሮፓጋንዳዎች ፤ ያልሆኑትን የሆኑ እስኪመስላቸው ድረስ፤ ትርጉም በሌለው ፉከራ እና ቀረርቶ አስተው የክልሉን ሕዝብ ብዙ ዋጋ አስከፍለዋል።

በጽንፈኛ አስተሳሰቦች ሰለባ ከሆኑ ዲያስፖራዎች፤ ጊዜ ካለፈባቸው ፖለቲከኞች፤ ሁሌም ከመቃወም የዘለለ የፖለቲካ ተሳትፎ ከሌላቸው የፖለቲካ ልሂቃን እና የዩቲውብ የግጭት ነጋዴዎች ጋር በመሆንም፤ የታሪካዊ ጠላቶቻችን አጀንዳ ተሸካሚዎች በመሆን አካባቢውን የግጭት ቀጠና አድርገውታል።

እነዚህን ኃይሎች አደብ በማስገዛትና የተገዙበትን የተሳሳተ/ጽንፈኛ አስተሳሰብ ለዘለቄታው በማረም የክልሉን ሰላም ለመመለስ በክልል ደረጃ ““ሰላም ለሁሉም ሁሉም ለሰላም” በሚል መሪ ሀሳብ እየተካሄዱ ያሉ ሕዝባዊ የሰላም ኮንፈረንሶች ከሁሉም በላይ የክልሉን ሕዝብ ከተሳሳቱ ትርክቶች እና ትርክቶቹ ከፈጠሯቸው ውዥንብሮች እና የሰላም እጦቶች መታደግ የሚያስችሉ ናቸው።

በተለይም ከሰላም እጦት ጋር በተያያዘ ብዙ ዋጋ ለመክፈል የተገደደውን የክልሉ ሕዝብ ለሰላሙ ዘብ እንዲቆም፤ ክልሉን ከጽንፈኛ የጥፋት ኃይሎች ለማጽዳት ለሚደረገው ሀገራዊ ጥረት ትልቅ አቅም የሚፈጥሩ ናቸው። የክልሉ ሕዝብ አብዝቶ የሚመኘውን ሰላም እና ልማት እውን ለማድረግም አስተዋጽኦአቸው የላቀ ነው!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የኮሪደር ልማት - የስኬትና የውበት ተምሳሌት

ደቤ ከደጃች.ውቤ

የኮሪደር ልማት በአብዛኛው የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን የሚያጠቃልል የማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስተጋብር የሚፈጥር፤ ውብና ማራኪ የከተማ ፕላንና የልማት ሂደት ነው። ለትራፊክ ለተጨናነቁ የመንገድ መሰረተ ልማቶችና ለከተማ ጽዳት ፍቱን መድህኒት ናቸው።

በኢትዮጵያ የኮሪደር ልማት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጠቅላይ ሚኒስትር ሀሳብ አመንጭነት በአዲስ አበባ ከተማ ተጀምሮ በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ ከተሞች እየተተገበረ ይገኛል። ልማቱ እንደ አሁኑ በስፋት ባይሰራበትም በጃንሆይ ዘመነ መንግስት እንደ አዲስ አበባ በመሳሰሉ ከተሞች ተግባራዊ ስለመደረጉ አንዳንድ መሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል።

በዚህም በዘመኑ የተገነቡ አንዳንድ ሕንፃዎችና የንግድ ቤቶች ኮሪደር ነበራቸው። ሰዎች መንገድ ለመሄድም ሆነ ለማረፍ የሚቸገሩበት ሁኔታ አልነበረም። ከመኪና መንገድ የራቁ ስለሆነ እግረኞችን ከትራፊክ አደጋ የሚጠብቁ በዝናብም ሆነ ፀሐይ እንዳይጠቁ የሚረዱ ነበሩ።

ብሔራዊ ቲያትር ኮሪደር እንዲኖረው ተደርጎ እየተሠራ ነው። በመርካቶ አንዋር መስኪድ አካባቢ በተለምዶ ፍራሽ ተራ በመባል የሚጠራ ብዙ ሱቆች ያሉት የንግድ ቦታ ኮሪደር ነበራቸው። በአውቶቡስ ተራ ወደ ሰባተኛ መንገድ በሚወስደው ቦታ በስተግራ የነበሩ በተለምዶ ወሎ ፈረስ የሚባል አካባቢ የነበሩ ሱቆች የራሳቸው ኮሪደር ነበራቸው።

አራት ኪሎም ብንመለከት የትምህርት ሚኒስቴር ሕንጻ ኮሪደር ልማቱ ሲጀመር መልሶ ሰዎች ክፍት ሆነ እንጂ በገነት ዘውዴ ሚኒስትርነት ዘመን ጀምሮ ለእግረኛ ዝግ ሆኖ ነበር። ጆሊ ባርን ተከትሎ ወደ ብርሃንና ሰላምና አምስት ኪሎ መንገድ የነበሩ ሕንፃዎች የራሳቸው ኮሪደር ነበራቸው። ይህ በቀደምት ሌሎች የሀገሪቱ ከተሞች ውስጥ በተመሳሳይ መልኩ የሚስተዋል ነው።

በተለያዩ ምክንያቶች ይህንን በመልካም ጅማሮ ማስቀጠል አለመቻላችን፤ከብዙ ዓመታት በኋላ ወደኋላ ተመልሰን ትናንት ልንሰራው የሚገባንን የቤት ስራ ለመስራት ተገድደናል። ከተሞቻችንን ካሉበት ሁለንተናዊ ኋላቀርነት ለመታደግ፤ በከተሞች ያሉ ዜጎቻችንን የአኗኗር ዘይቤ ለመቀየር አሁን ላይ እየከፈልነው ያለውን ዋጋ እንድንከፍል ሆነናል።

የለውጡ መንግስት ወደ ስልጣን በመጣበት ወቅት ለሕዝብ ቃል ከገባቸው ጉዳዮች መካካል አንዱ ከተማን ለነዋሪዎች ምቹና ተስማሚ ውብ ከተማ ማድረግ ነው። ከተሞችን መሰረተ ልማቶች በማሳደግ የነዋሪዎችን ሕይወት የሚያቀሉ ልማቶችን ማከናወን፤ የከተሞችን ደረጃ በማሳደግ ገቢ የማመንጨት አቅማቸውን ማሳደግ ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በአዲስ አበባ በመጀመሪያው ዙር በተካሄደው የኮሪደር ልማት የተገኙ ስኬታማ ተሞክሮዎች፤ አንድም መንግስት ለሕዝቡ የገባውን ቃል ለመፈጸም ያለውን ቁርጠኝነት በተጨባጭ ያመላከተ ነው። ከዚህም ባለፈ እንደ ሀገር በልማት ዙሪያ አዲስ ሀገራዊ የስራ ባህልንና ፕሮጀክቶች በአጭር ጊዜ የመፈጸም አቅም መፍጠር ያስቻለ ነው።

ከተማዋንን እንደስሟ አዲስ ለማድረግ የተደረገው አሁናዊ ጥረትም ብዙዎችን ያስደመመ ነው። ከፒያሳ-አራት ኪሎ፤ ከአራት ኪሎ- መገናኛ፤ ከመስቀል አደባይ-ቦሌ፤ ከሜክሲኮ- ሳር ቤት፤ ከመገናኛ ሰሚት፤ ከፒያሳ ቸርችል ያለውን የኮርደር ልማት ገጽታን ከዓመት በፊት ከነበረው ገጽታ ጋር በማነጻጸር ማየት የልማቱን ፋይዳ መናገርና ምስክርነት መስጠት አያሻም።

ከአፍሪካ መዲና፤ ከዓለም አቀፍ ዲፕሎማቶች መቀመጫ አዲስ አበባ የተወጠነው የኮሪደር ልማት በክልል ከተሞችና በዞን ከተሞች ጭምር በስፋት ተግባራዊ እየሆነ ነው። ለምሳሌ በደብረ ብርሃን ከተማ በ500 ሚሊየን ብር፤ ሰባት ኪሎ ሜትር የኮሪደር ልማት እየተሠራ ነው።

ልማቱ ከተማዋን ስማርት ሲቲ እና ለነዋሪዎቿ ምቹ ለማድረግ የሚረዱ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን ያካተተ ነው። በአዲሱ በጀት ዓመት መጀመሪያ የተጀመረው የኮሪደር ልማቱ በበጀት ዓመቱ ተጠናቆ ለሕዝብ ክፍት እንደሚሆን ይጠበቃል።

> **ከአፍሪካ መዲና፤ ከዓለም አቀፍ ዲፕሎማቶች መቀመጫ አዲስ አበባ የተወጠነው የኮሪደር ልማት በክልል ከተሞችና በዞን ከተሞች ጭምር በስፋት ተግባራዊ እየሆነ ነው። ለምሳሌ በደብረ ብርሃን ከተማ በ500 ሚሊየን ብር፤ ሰባት ኪሎ ሜትር የኮሪደር ልማት እየተሠራ ነው**

በተመሳሳይ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በጎንደር የተጀመረው የመጀመሪያው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት የዐፄ ፋሲል ቤተመንግሥት እድሳትን ጨምሮ በከተማዋ አንድ ነጥብ ስምንት ኪሎ ሜትር የሚሸፍን የኮሪደር ልማት እየተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም በጥሩ ደረጃ ይገኛል። በከተማው ሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት በያዝነው በጀት ዓመት ሁለተኛ ሩብ ዓመት ተጀምሯል። የኮሪደር ልማቱ የጎንደር ጥንታዊነትና ታሪካዊነት በጠበቀ መልኩ እየተከናወነ ስለመሆኑ ከሰሞኑ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትሯ ወይዘሮ ሰላማዊት ካሳ በጎንደር ተገኝተው ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት ተናግረዋል።

በጎንደር ሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት 12 ኪሎ ሜትር የመንገድ ክፍል የሚለማ ይለማል፤ ከፒያሳ- አዘዞ፤ እስከ አየር ማረፊያ ያለውን የከተማ ቦታ የሚሸፍን ሲሆን የዲዛይን ሥራው ተጠናቆ ወደ ትግበራ ተገብቷል። ለዚህም የመንገድ ዳር ኮንቴይነሮችንና አጥሮችን የማንሳት ሥራ እየተከናወነ ስለመሆኑ የከተማዋ አስተዳደር ገልጧል። ተነሺዎችም በሦስት ክላስተሮች በተደራጁ ቦታዎች ዳግም ሥራ እንዲጀምሩ ማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትም እየተከናወኑ ነው።

የጎንደር ከተማው ኮሪደር ልማት እንደ አዲስ አበባ ከተማ ሕንፃዎችን የማስዋብ፣ የእግረኛና የብስክሌት መንገዶችን የመገንባት እንዲሁም መንገድ ዳር መብራቶችን የመትከልና የአስፋልት ማንጠፍ ሥራዎችን ያካተተ ነው። የአረንጓዴ ስፍራዎችና የመዝናኛ ፓርኮች ግንባታን፤ የመብራት፣ የውሃ፤ የስልክና የኢንተርኔት መስመሮችም አንድ ወጥ በሆነ መንገድ መዘርጋት የሚያስችል አሰራርን የተከተለ ሲሆን በኮሪደር ልማት የታወቁት ቻይናና የአፈሪካዋ ሀገር ሩዋንዳ ምሳሌ ናቸው፡፡

የጎንደር የኮሪደር ልማት በጥር ወር በታላቅ ኃይማታዊና ባህላዊ ሥርዓት ለሚከበረው የጥምቀት በዓል በልዩ ድባብ ለማክበር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር፤ ለከተማው የቱሪስት ፍሰት ማደግም አዎንታዊ ሚናው ከፍያለ እንደሆነ ይታመናል። በአጠቃላይ በከተሞቻችን እየተካሄደ ያለው የኮሪደር ልማት አዲስ የሥራ ባህል የፈጠረ ነው።

በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ የሥራ መነሳሳትን ያጫረ፤ ለበርካታ ወገኖች የሥራ እድል መፍጠር ያስቻለ ፕሮጀክት ነው። ወጣቱ በፈረቃ ጠዋትና ማታ ሥራዎችን በቅልጥፍና በጥራት አስውቦ ለመጨረስ ያለው ተነሳሽነት በራሱ የሚያኮራ እና ይበል የሚያሰኝ ነው።

በቀጣይ በከተሞች ለሚከናወኑ ግንባታዎች መልካም ተጨባጭ ተሞክሮ ነው። ስራው አለቃና ምንዝር ተናበው የሠሩበት፣ መንግሥት ትኩረት የሰጠበት፣ ክትትል ያደረገበት፣ ለሌሎች የመንግሥት ፕሮጀክቶች፤ ለከተሞች የኮሪደር ልማቱ የስኬትና የውበት ተምሳሌት ነው፡፡

እንደ ሀገር በተጀመረው የኮሪደር ልማት የታየው መነሳሳት፤ ስራን በጥካሬና ሰው አይቶ በሚመሰክረው ልክ እንደተሰራ ሁሉ በተመሳሳይ በሌሎች ሀገራዊ ግዙፍ ፕሮጀክቶችም ይህንኑ መተግባር የሚያስችል አቅም ማጎልበት፤ለዚህ የሚሆን ቁርጠኝነት መፍጠር ተገቢ ነው።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

## ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# የሀገር መልኩ - ሕብረብሔራዊ ቀለም ነው

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽከታብ)

ሀገር የብዙሀነት ጥርቅም ናት። ብዙሀነት ደግሞ የልዩ ልዩ ቋንቋዎች፣ ባህሎችና ታሪኮች፣ እሴቶችና ልማዶች ነጸብራቅ በመሆን ይገለጻል። ሀገር የሚለው ግዙፍ የወል ስምም ይሄን የልዩነት አጥር ታኮ የቆመ የብዙሀነት ስያሜ መሆኑ አያከራክርም። በየትኛውም የዓለም ጫፍ ሀገርና ሕዝብ በዚህ ትርጓሜ በኩል የሚገለጹ መሆናቸው እሙን ሲሆን በብዙ ልዩነት ውስጥ ደምቀንና ፈክተን የምንታየው የጋራችን በሆነች ኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑ እንደዚሁ የሚያስማመን ነው፡፡

ሀገር የሚለው ሶስት ቃል ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በክብር ተሸክሞ ሶስት ሺ ዘመናትን በድልና በሉአላዊነት ተሻግሯል። ይሄ ግዝፈት እንዴት መጣ? እንዴትስ ጸና? እንዴትስ ሳይንገዳገድ በብዙ ዘመን ውስጥ ተሻገረ ብለን ብንጠይቅ የምናገኘው ምላሽ ኢትዮጵያዊ ትስስርን ነው። በእውነቱ ትስስራችን የሚገርም ነው።

ኢትዮጵያዊነት ውስጥ ከሚያስደንቁኝ ባህሎች አንዱ የእርስ በርስ ጉርብትናችን፣ ትብብራችን፣ መቻቻላችን ሲሆኑ አሁን ላይ እነዚህ ውብ ትውፊቶቻችን በመጥፎ ትርክት መደብዘዛቸው እንደዚሁ የሚያስቆጨኝ ነው። የዚህ ጽሁፍ ዋና ዓላማም እነዚህን የጋራ እሴቶቻችንን ከጥቃት በመጠበቅ በአብሮነት ስም ማስቀጠል ነው፡፡

ስለሀገርና ሕዝብ ያጠኑ፣ የጻፉ፣ የተጠበቡ ልሂቃን ሀገር የሚለውን ሰፊ ግዛት ከብዙሀነት የታሪክ ውርርስ ጋር ያነካኩታል። ይሄ ማለት ከፍ ብዬ እንዳልኩት ከግለሰብ እስከ ማህበረሰብ በሚወርድ የጉርብትና ተዋረድ መንጭቶ የሚፈስ እንደሆነ ይመሰክራሉ። እንደዚሁም ስለለውጥና ስኬት የሚያጠኑ ዓለም አቀፍ ባለሙያዎች ሀገራዊ ለውጥ በግለሰባዊ ለውጥ ውስጥ እንዳለ እና እድገትና ዘመናዊነት የሚባሉት ማህበራዊ መሻቶች ከጤናማ ዜጋ፣ ከጤናማ ትውልድ፣ ከጤናማ የፖለቲካ እሳቤ እንደሚጀምርም አጽንኦት በመስጠት ሀሳባቸውን ያጋራሉ።

ጤናማ የሚለውን ሀሳብ ከብዙ አቅጣጫ ልናየው ብንችልም ከተነሳንበት የሀገርና ሕዝብ ጽንሰ ሀሳብ አኳያ ግን ከሰላምና ከደህንነት ጋር ልናቆራኘው እንችላለን። እንደሚታወቀው የሀገራችን አሁናዊ ሁኔታ በብዙ መልኩ የሰላም ጥያቄ የሚነሳበት ነው። የሰላም ጥያቄ ብዙ መነሻ ቢኖረውም በተረጩ የትርክት መርዞች የደፈረሰ እንደሆነ ብናገር ልክ እሆናለው። የረገቡና የላሉ የሕብረብሄራዊነት ቋጠሮዎቻችን በፖለቲካ የሚመዘኑ፣ በዘርና በብሄር የሚተመኑ አይደሉም። ሰውነትንና ተፈጥሮን መሰረት አድርገው ስለአብሮነት እንዳይላሉ ሆነው የጠበቁ እንጂ ሲፈልጉ የሚላሉና የሚጠብቁ አይነት አይደሉም፡፡

የጥላቻ ትርክት እንዳይለያየን ለሰላም ቅድሚያ መስጠት፣ ለአብሮነት እድል መስጠት፣ በመነጋገርና በመወያየት ልዩነትን ማጥበብ ቀዳሚ መፍትሄዎቻችን ናቸው። ሰላም ለናፈቀው ማህበረሰብ ሰላም ሰባኪ ድምጾች ያስፈልጉታል። የትናንት ታሪኮችን አጽመ ታሪክ እየበረበሩ በወንድማማች መሀል ጠብን መዝራት ለማንም የማይጠቅም የዝቅታ መገለጫ ነው። ዓላማችን ኢትዮጵያን ከፍ ማድረግ ከሆነ በሀሳብና አሁናዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እናተኩር። ሰላም ትናንትን በመዘከር አይመጣም። ልማት ያለፈን በመውቀስ አይረጋገጥም። ችግሮቻችን በዛሬ የሀሳብ የበላይነት የሚረግቡ እንጂ የትናንት ስህተቶችን በማስታወስ የሚመክኑ አይደሉም። ሀገራችን ኢትዮጵያ ከምንም በላይ በሀሳብ የደለበ ጤነኛ ዜጋ፣ ጤነኛ ትውልድ፣ ጤናማ ፖለቲከኛ ትፈልጋለች፡፡

ፖለቲካው ካልዘመነ ሀገራችንን ማዘመን አንችልም። በአንድ ሀገር ላይ የፖለቲካ ድርቀት ሀገርን ለማቀንጨር የሚደርስበት የለም። የፖለቲካ ዝማኔ ደግሞ ከሀሳብ የሚወለድ፣ ለሀሳብ ያደላ፣ ስለሀሳብ የሚመክር ነው። በሀሳብ ካልዘመንን በጦርነት ሰልጥነን ገዳይና ሟች በመሆን በነውር መጠራታችን ይቀጥላል። በሀሳብ ካልሰለጠንን በትናንት ስህተት ዛሬን ማበላሸትና ለነገ ቁርሾ ማስቀመጥ ግብራችን ይሆናል፡፡

ዝማኔ የሀሳብ ብስለት ነው። ዝማኔ ወደ ጨለማዎች ብርሀን መርጨት ነው። ዝማኔ ለብዙሀን ውጋግ መሆን ማለት ነው። የሀገር መልክ የሕብረብሄራዊነት ቀለም ነው ብዬ መነሳቴ በእንዲህ አይነቱ ሰላምና እርቅን ባስቀደመ የወንድማማችነት አካሄድ እንጂ በይዋጣልን አይደለም። አንድም ሰው የሌለባት ሀገር ታውቃላችሁ? ጤነኛ ፖለቲካ የሌለባት ሀገር አንድ ሰው እንደሌለባት ሀገር ናት። ሰላም የራቀው ሕዝብ፣ በጥላቻና በቁርሾ የተዘባነነ ትውልድ በብዙሀነት ውስጥ በምንምነት የሚጠራ ነው። ትግላችን ሊሆን የሚገባው በጤናማ ፖለቲካ ጤናማ ሀገር መፍጠር ነው። ጤናማ ፖለቲካ ደግሞ ከአሰላሳይና ነገን አርቆ ከሚያስተውል ልቦና የሚሰራ ነው፡፡

> ራስን መቀየር ስንል በብስለት፣ በስክነት በብልህነት መቆም ማለት ነው። የማይጠቅሙ አስተሳሰቦችን፣ ልማዶችን፣ የኑሮ ዘይቤዎችን መቀየር ማለት ነው። የተግባቦት ስኪልን ማሳደግ፣ ለጋራ ጥቅም በጋራ ማበር፣ በሀገር ጉዳይ ላይ የያገባኛል ስሜትን መፍጠር የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል

በጥላቻ እዛና እዚህ የጎሪጥ በሚተያይ ማኅበረሰብ ውስጥ ሀገር የለችም። ብትኖርም በብዙሀነት መሀል እንደምንም ነን። ብዙሀነት ዋጋና ትርጉም ያለው በመዋደድና በመፋቀር፣ በመቻቻልና በመከባበር ውስጥ ነው። ለተነሳሁበት ዓላማ እና ላለንበት ሀገራዊ ውጥንቅጥ መፍትሄ በመሆን ተስፋ የሚሰጠን ጤነኛ ፖለቲካን በጤነኛ ፖለቲከኞች መገንባት የሚለው ነው። ሰላም የቀደመበት የትኛውም ጉርብትና ጤናማ ነው። ሀገር እና ማኅበረሰብ ከፖለቲካ መንጭተው ወደነገ የሚሄዱ ፈለግና ዳና በመተው ትውልዱ ላይ የሚያርፉ ዐሻራዎች ናቸው፡፡

ትናንትና በሰላም ካልመጣን ዛሬን በሰላም ለመኖርና ነገን በሰላም ለመቀበል መበርታት የእኛ ኃላፊነት ነው። ብዙዎቹ ጠበብት ‹የሀገርን ለውጥ ከግለሰብ ለውጥ ጋር፣ የትውልድን ለውጥ ደግሞ ከሀገር ለውጥ ጋር ያቆራኙታል። ከእኛ በቀር ሁሉም የዓለም ሕዝብ ይሄን እውነት ያውቃል። ወደ እኛ ሀገር ስንመጣ የለውጥ መሰረት ምን እንደሆነ ገና የገባን አይመስለኝም። ምክንያቱም ከትናንት እስከዛሬ የተራመድንባቸው ጎዳናዎች የለውጥን ሕግ የሳቱ መሆናቸው ነው፡፡

ዛሬም ድረስ እያደረግነው ያለው ነገር ከለውጥ ሕግ ጋር የሚቃረን መሆኑ ነው። ራሳችንን ሳንቀይር ሀገር ለመቀየር የቆምን ብዙዎች ነን። በአንድ ሀሳብ ሳንስማማ ሀገር ለመቀየር የፖለቲካ ፓርቲ አቋቁመን የምረጡኝ ቅስቀሳ የምናደርግ ብዙዎች ነን። ተነጋግረን ሳንግባባ ደጋፊና ተከታይ አቋቁመን የነገዋ የኢትዮጵያ ተስፋ ስንል ለራሳችን የማይገባ ስም ሰጥተን የምንቀሳቀስ ሞልተናል።

በዘርና በጎጥ ተቧድነን ስለኢትዮጵያዊነት ለመናገር ድፍረት ያለንም አለን። እኚህ አካሄዶች ምን ያክል አደገኛ እንደሆኑ ከደረሱብንና እያደረሱብን ካለው መከራ ለመታዘብ ችለናል። አሁንም በዛ መንገድ የምንጓዝ አለን። ይሄን መጥፎ ታሪክ ከመድገም ባለፈ ታሪክ አይቀይርም፣ ታሪክ አያድስም። የለውጥ ሕግ አልገባንም ስል መናገሬም ለዚህ ነው። እውነተኛ ለውጥ ራስን ከመቀየር፣ አስተሳሰብን ከማዘመን የሚነሳ ነው። እድገት ስልጣኔ ከእኔ ወደ ሌላው፣ ከሌላው ወደ እኔ ከዛም ማህበረሰብ ላይ የሚያርፍ ነው።

ራስን መቀየር ስንል በብስለት፣ በስክነት በብልህነት መቆም ማለት ነው። የማይጠቅሙ አስተሳሰቦችን፣ ልማዶችን፣ የኑሮ ዘይቤዎችን መቀየር ማለት ነው። የተግባቦት ስኪልን ማሳደግ፣ ለጋራ ጥቅም በጋራ ማበር፣ በሀገር ጉዳይ ላይ የያገባኛል ስሜትን መፍጠር የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል። ራስን መቀየር ማለት ከራስ በፊት ለሀገርና ሕዝብ የሚያስብ ሰውነትን መፍጠር በሚለውም ይገለጻል። እኛ ደግሞ እኚህ ሁሉ የሉንም። እኚህ ሁሉ በሌሉበት ነው ሀገር ለመፍጠር የምንፍጨረጨረው፡፡

መጀመሪያ ራሳችንን እንቀይር። ግለሰብ ሳይሰለጥን ሀገር አትሰለጥንም። ዜጋ ሳይለወጥ ሀገር አትለወጥም። መጀመሪያ እኛ እንለወጥ። መጀመሪያ አስተሳሰባችንን እንግራ። በእውቀት፣ በአንድነት መንፈስ መተባበርን ልማድ እናድርግ። ከዚህ እውነት ቀጥሎ ነው የሀገር ለውጥ የሚመጣው። ራሳችንን በጥላቻ፣ በመለያየት እያኖርን ብልጽግናን መጠበቅ ሞኝነት ነው። ራሳችንን ከአንድነት፣ ከወንድማማችነት አርቀን ስልጡን ሀገርና ሕዝብ መጠበቅ የማይታሰብ ነው፡፡

ጎዳናዎቻችን በደም የጨቀዩ አንድ አይነቶች ናቸው። ለሀሳብ ሳይሆን ለጸብ፣ ለእርቅ ሳይሆን ለትንቅንቅ እንድንመች ሆነን የቆምን ነን። የተቀየረ ምንም ነገር የለንም። ይሄ ማለት ራሳችንን አልቀየርንም፣ ፖለቲካውን አላዘመንም ማለት ነው። ይሄ ማለት ትናንታችንን አልረሳንም ማለት ነው። ለዛ ነው መለወጥ ያልቻልነው። በዚህም አልን በዚያ ግለሰባዊ ለውጥ የምንም ነገር ወሳኝ ነው። ፖለቲካው ወደ ሕዝብ ሕዝብም ወደ ፖለቲካው የሚያዩበት ጊዜ እስካልመጣ ድረስ የደም ፖለቲካን፣ የይዋጣልን ታሪኮቻችንን ማደስ አንችልም፡፡

በምድር ላይ አንደኝነትን የሚሹ በርካታ ነፍሶች ተፈጥሮዋል። ሁላችንም ለብኩርና የምንጋፋ ነን። ሁላችንም አንደኛ ለመሆን የምንኖር ነን። በሌላ መንገድ የሁሉም የሰው ልጅ ፍላጎት አንደኛ መሆን ነው እያልኩ ነው። ለማሸነፍ የማንፈነቅለው ድንጋይ የለም። ለመብለጥ የማናደርገው የለም። የማሸነፍን ጥቅምና ዋጋ ያወቅነውን ያክል እንዴት ማሸነፍ እንዳለብን የምናውቅ ግን ጥቂቶች ነን። ለዚህም ነው ሕልመኞች ሆነን የቀረነው። ለዚህም ነው ከሙላታችን ጎላን የቆምነው። ማሸነፍ የማሰብ ውጤት ነው። አንደኝነት ከሩጫ ባለፈ የእውቀትና የአስተውሎት ጎዳና ነው።

እግሮቻችንን ሩጫ ሳናስለጥን ለሩጫ የሚሆን ጥሩ ጫማ ብንገዛ ዋጋ የለውም። እጆቻችንን ስራ ሳናስለምዳቸው ብዙ እቅድ ብናወጣ ጥቅም የለውም። ልቦቻችንን እውነት ሳናስተምራቸው ጥሩ ለብሰን ለውድድር ብንቆም ትርፍ የለውም። ፖለቲካችን ሀገርና ሕዝብ ሳይገቡት ለሀገርና ሕዝብ የቆምኩ ነኝ ቢል ዋጋ የለውም። ከሀሳብ እንጀምር፣ በሀሳብም እናብቃ። በሁለት እግራችን መቆም ባቃተን በዚህ አስቸጋሪ ዘመን ላይ በሀሳብ ጀምሮ በሀሳብ እንደማብቃት ያለ ጀግንት የለም። ራሳችንን አድሰን ለነጋችን ዋስትና፣ ለሀገራችን ደግሞ የመፍትሄ አካል መሆን በምንም የማናድበሰብሰው አበይት ጉዳያችን ሊሆን የሚገባው ነው፡፡

አብዛኞቹ ችግሮቻችን እኛው የፈጠርናቸው ናቸው። ችግሮቻችንን በገዛ እጃችን ስንፈጥር ለፈጠርናቸው ችግሮች የሚሆን መፍትሄ ግን የለንም። የሰው ልጅ አእምሮውን በሚገባ ከተጠቀመ ችግሮቹን በቁጥጥር ስር ማድረግ አያቅተውም። ይሄ ተፈጥሮአዊ እውነት ነው። በትንሽ አእምሮ ትልቅ ችግር የመፍጠርን ያክል አሳፋሪ ነገር የለም። እየሆነብን ያለው ደግሞ ይሄ ነው። በማሰብ ፈርጥመን በትልቅ ኃይል ችግሮቻችንን መርታት እስካቻልን ድረስ ከወሬ ባለፈ ቁም ነገር አይኖረንም። በሀሳብ ከፈረጠምን እጅ የሚሰጠን እንጂ እጅ የምንሰጠው ችግር አይኖረንም። እስካሁን ካለመነጋገር በስሜት ለችግሮቻችን እጅ ስንሰጥ ከርመናል። ቀሪው ጊዜ ችግሮቻችን እጅ ሰጥተው፣ ጦርነትን ሽረን፣ ሰላምን አውርደን፣ ወንድማማችነታችንን የምናስቀጥልበት እንዲሆን ኃላፊነት ወድቆብናል፡፡

ሀገር ታማኝና ለለውጥ የበረታ ዜጋ ከሌላት ዋጋ የላትም። ሀገር ለእርቅ ልቡን፣ ለድርድር በሩን የከፈተ መንግስትና ሕዝብ ከሌላት ተስፋ የላትም። በአንድ ሀገር ላይ ሁሉም እድሎች፣ ሁሉም ስኬቶች በግለሰብ ለውጥ የተፈጠሩ ናቸው። ሀገራችንን ለተሻለ ነገር የምናበቃት እኛ ነን። ሕይወት የምትሰምረው ዝም ብሎ በመኖር ሳይሆን እንዴት መኖር እንዳለብን ስንረዳ ነው። በዚህ መረዳት ውስጥ ነው አሸናፊነት።

እንደ ዜጋ በሕይወት ሩጫ ውስጥ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት ባለ ራዕይ መሪና ተመሪ መሆን ያስፈልጋል። እንደ ሀገር የተሻለ ኢኮኖሚ ለመገንባት ደግሞ ከትናንት የተሻለ ዘመኑን የዋጀ አስተሳሰብ ግድ ይለናል። አሸናፊ ለመሆን ከፍላጎት በላይ ጽናት ያስፈልጋል። ነገሮችን በተለየ መልኩ ማየት ግድ ይላል። ችግሮቻችን የበረቱብንም ከችግሮቻችን የገዘፍን ሆነን ስላልተገኘን ነው። ሀገራችንን ለመለወጥ በምናደርገው ትግል ልክ በሀገር ጉዳይ ላይ ስንግባባና አንድነት ሲኖረን አይታይም፡፡

ከአምና እና ካቻምና እንውጣ። የዓለም ስልጣኔ የአንድነት ስልጣኔ ነው። እንደ ሀገርም እንደ ሕዝብም ከትላንትነት ውስጥ አልወጣንም። ለአንደኝነት ባላበቃን ትናንት ውስጥ ምን እናደርጋለን? አሸናፊነት የልምድና የተሞክሮ ውጤት ነው። አንደኝነት የፍቅርና የመቻቻል ነጸብራቅ ነው። እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ግለሰብ ፍቅርን ማወቅ ብዙ ትርፍን ያመጣልናል። ፍቅር አጥተን በጥላቻ እየኖርን የምናመጣው የጋራ ድል የለም፡፡

ሰው ፍቅር ከሌለው ደስታ የለውም። ሕዝብ አንድነት ከሌለው እድገት የለውም። ጉዳችንን አያችሁት? እናድግ ዘንድ፣ ከፍ እንል ዘንድ ፍቅር እና አንድነት ያስፈልጉናል። ዓለም ላይ ከኢኮኖሚ ባለፈ የደስተኝነትን ክብር ያገኙ ሀገራት ፍቅርና አንድነትን ያስቀደሙ ናቸው። ከትናንት እስከዛሬ በማሸነፍ ዓለም ውስጥ የሚኖሩ እነሱ በፍቅር ኃይል ራሳቸውን ያደሱ ናቸው። ፍቅር የመጨረሻው ደህንነታችን ነው፡፡

ይሄ ዓለም በፍቅር ኃይል እንደሚመራ ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? የምንፈልገው ጥሩ ነገር ሁሉ የእኛ የሚሆነው ልባችን ውስጥ ባለው ፍቅር ልክ እንደሆነስ ስንቶቻችሁ ገብቷችኋል? መልካምም ይሁን መጥፎ የምትፈልጉት ነገር ሁሉ በፍቅርና በጥላቻችሁ የሚሳብ ነው። እስከዛሬ ያላሸነፍነው በጥላቻ ልባችን ለማሸነፍ ስለሮጥን ነው። እስከዛሬ አንደኛ ያልወጣነው ይቅርታ በሌለው ልብ ስለተወዳደርን ነው። እስከዛሬ ነግደን ያላተረፍነው፣ ተምረን ስራ ያልያዝነው፣ ኖረን ለቁም ነገር ያልበቃነው የፍቅርን ኃይል ስላልተረዳን ነው። ሀገር ፍቅር ትሻለች። ሀገር ይቅር የሚል ልብ ያስፈልጋታል። ለዚህም ነው ራሳችንን እናድስ፤ የሀገር መልክ የሕብረብሄራዊነት ቀለም ነው ብዬ መጀገኔ።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የዓሳ ሃብት ልማትን የማሳደግ አበረታች ጥረቶች

ማህሌት አብዱል



ዶ/ር ጋሻው ተስፋዬ



ኢትዮጵያ እምቅ የዓሳ ሃብት ባለቤት መሆኗን ጥናቶች ያሳያሉ። ከሀገሪቱ ወንዞች፣ ሐይቆች፣ ኩሬዎችና ሌሎች የውሃ አካላት በዓመት ከ94 ሺ 500 ቶን በላይ የዓሳ ምርት ማግኘት እንደሚቻል ጥናትን ዋቢ ያደረገው የግብርና ሚኒስቴር መረጃ ያመለክታል። ይህንን ሃብት ጥቅም ላይ በማዋል ረገድ ግን ሰፊ ክፍተት መኖሩ ይጠቀሳል። የሕብረተሰቡ ዓሳን የመመገብ ባህል ደካማ መሆን ሀገሪቱ ከዚህ እምቅ ሀብት የሚገባትን ጥቅም እንዳታገኝ አድርጓት መቆየቱ ይገለጻል።

መንግሥት የምግብ ዋስትናንና የምግብ ስርዓትን ለማረጋገጥ በነደፈው የሌማት ትሩፋት መርሃ ግብርም ሆነ በግብርና ፖሊሲው ልዩ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች አንዱ የዓሳ ግብርና ነው። ለእዚህም ዓሳን ማዕከል ያደረጉ የተለያዩ ስትራቴጂና የሕግ ማሕቀፎችን በማዘጋጀትም ዘርፉን ለማሳደግ ጥረት እየተደረገም ይገኛል፡፡

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ብሔራዊ የዓሳና የውሃ ውስጥ ሕይወት ምርምር ማዕከል ዳይሬክተር ዶክተር ጋሻው ተስፋዬ በተለይ ለአዲስ ዘመን ፤ በኢትዮጵያ 200 የሚደርሱ የዓሳ ዝርያዎች መኖራቸውን ጥናቶችን ዋቢ አርገው ገልጸዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ ከዚህ ውስጥ ደግሞ 190 የሚሆኑት ሃገር በቀል ሲሆኑ፣ ከእነዚህ መካከልም 45ቱ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ናቸው። ይሁንና ከእነዚህ ውስጥ ሕብረተሰቡ ለገበያና ለምግብነት የሚጠቀምባቸው ቆሮሶ፣ ነጭ ዓሳ (ናይል ፐርች) አምባዛና ዱባ የተባሉ በጣም ውስን የሆኑትን ዝርያዎች ብቻ ነው፡፡

"ኢትዮጵያ የምስራቅ አፍሪካ የውሃ ማማና ሰፊ የዓሳ ሃብት ባለቤት እንደመሆኗዋ ከዘርፉ የሚገባትን ያህል ተጠቃሚ ያለመሆኗዋ ቁጭት የሚፈጥር ነው" የሚሉት ዳይሬክተሩ፤ የዚህ ዋነኛ ምክንያትም የሕብረተሰቡ የአመጋገብ ባህል እንደሆነ ይገልጻሉ። በተለይም ከእምነት ጋር ተያይዞ ባለ አመላካከት ሃብቱ ባለባቸው አካባቢዎችም ሳይቀር ዓሳን በምግብነት የሚጠቀመው የሕብረተሰብ ክፍል ውስን መሆኑን ይጠቅሳሉ። በሌላ በኩል ግን በተለይም በከተሞች አካባቢ የተመጋቢው ቁጥር ከፍ ቢልም ዓሳ እንደልብ የማይገኝ መሆኑ ሃብቱ ጥቅም ላይ እንዳይውል ያደረገው መሆኑን ያመለክታሉ።

ይህም ቢሆን ግን የውሃ አካልን ተጠግቶ በሚኖረው ሕብረተሰብ ዘንድ ዓሳን የመመገብ ባህሉ ከፍ እንደሚል ዶክተር ተስፋዬ ይናገራሉ። አብነት አድርገውም በጋምቤላ 30 እና ከዚያ በላይ የሚሆኑት የዓሳ ዝርያዎች ለምግብነት እንደሚውሉ ይገልጻሉ። "ወደ ኦሞና ቱርካና ሃይቅ አካባቢ ያሉት የደቡብ ኦሞ አካባቢ ማህበረሰቦችም እንደዚሁ ሰፊ የዓሳ ዝርያዎችን ተመጋቢዎች ናቸው፤ ከስምጥ ሸለቆዎቹ ሃዋሳ፣ ዝዋይና አርባ ምንጭ ሃይቆች ከሰባት የሚልቁ የዓሳ ዝርያዎች ለገበያ ይቀርባሉ" ሲሉ ያስረዳሉ።

እስካሁን በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶችን መሰረት አድርገውም ‹ኢትዮጵያ ካሏት የተፈጥሮ የውሃ አካላት ብቻ ከ128 እስከ 130 ሺ ቶን አሳ በዓመት ማምረት የሚያስችል አቅም እንዳላት ዳይሬክተሩ ያነሳሉ። "የግብርና ሚኒስቴር ከሁለት ዓመት በፊት በወጣው መረጃ እንደሃገር በዓመት እየተመረተ ያለው ከ73 ሺ ቶን አይበልጥም፤ ይህም ያለንን ሃብት ሙሉውን መጠቀም አለመቻላችንን ያሳያል" በማለት ያብራራሉ። ሃብቱ ጥቅም ላይ ላለመዋሉም ሆነ ምርታማነቱ እንዳይጎለብት ካደረጉትና ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች በተጓዳኝ የአመራረት ሂደቱ ኋላቀርና ባህላዊ መሳሪያዎች ላይ የተንተራሰ መሆኑ ዋነኛው ተግዳሮት እንደሆነ ያስገነዝባሉ።

‹‹ለዚህ በዋናነት እንደ ችግር ሊነሳ የሚችለው የማስገሪያ መሳሪያዎቻችንን ኋላቀርና ባህላዊ መሆን ነው። ዘመናዊ የሚባሉ መሳሪያዎች ከውጭ የሚገቡ መሆናቸው እንደልብ ለማግኘት አዳጋች ነው›› በማለትም ይናገራሉ። በሕገወጥ መንገድ ከውጭ ገብተው ገበያ ላይ የሚታዩት ማስገሪያዎችም የዓሳ ሃብቱን የሚያመናምኑ መሆናቸውን ያስረዳሉ። በተለይም ዓሳ አስጋሪዎች በብዛት የሚጠቀሙት ተጎታች መረብ የተባለው መሳሪያ ዓሳዎች በሚራቡበት የውሃ ዳርቻ የሚቀመጥ በመሆኑ ወላድና ጫጩት ዓሳዎችን የሚያጠምድ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህም ተተኪ ዓሳ እንዳይኖር እያደረገ መሆኑን ያብራራሉ።

በዚህም ምክንያት እንደዝዋይና ጫሞ ባሉ ሃይቆች ላይ ያለው የዓሳ ሃብት በከፍተኛ መጠን መቀነሱን ያመለክታሉ። "ለምሳሌ ጫሞን ብንወስድ ከአራት ሺ ቶን በላይ በዓመት ይመረት ነበር፤ ዝዋይም ከሁለት እስከ ሶስት ሺ ቶን ዓሳ ይመረት ነበር። አሁን አንድ ሺ ቶን አካባቢ ነው የሚመረተው" ሲሉ ገልጸዋል፡

ከዚህ ባሻገርም በአሁኑ ወቅት ዓሳ በሚመረትባቸው በውስን ሃይቆች ላይ ያለው የአስጋሪው መጠን በከፍተኛ ደረጃ መጨመሩን ይናገራሉ። በሃይቆቹ ላይ የሚደረግ ምንም አይነት ቁጥጥርና ለአጥማጁ የሚሰጥ ፈቃድ ባለመኖሩ የሃይቆቹ ስነሕይወት ጭምር አደጋ ላይ የወደቀበት ሁኔታ መኖሩን ያስረዳሉ። ይህም ችግር በተለይ ዝዋይ፣ ሃዋሳና ጫሞ ሃይቆች ላይ ጎልቶ እንደሚታይ ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩልም ከፋብሪካ የሚወጡ ኬሚካሎች በሚያደርሱት ተፅዕኖ ምክንያት ምርቱ የሚቀንስበት ሁኔታ እንዳለም ይጠቁማሉ። "በተለይም ከአበባ እርሻዎች የሚወጡ ኬሚካሎች ሳይጣሩ ተመልሰው ወደ ሃይቅ የሚለቀቁበት ሁኔታ ይታያል፤ ይህም በጫጩቶችና የዓሳ እንቁላሎች ላይ ተፅዕኖ ስለሚያሳድር የሚፈለፈሉት የዓሳ ጫጩቶች አነስተኛ እንዲሆኑ አድርጓል" ይላሉ። እንደ ዝዋይ ባሉ ሃይቆች ዙሪያ የሚካሄደው የመስኖ ልማት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄዱን ጠቅሰው፣ ይህም የሃይቆቹ ውሃ መጠን እንዲቀንስ አደርጎታል፤ ይህም በውሃ ውስጥ ላሉ ስነ ሕይወቶች ሕልውና ስጋት ነው ሲሉም አስገንዝበዋል።

ዶክተር ተስፋዬ ዘርፉን ለማሳደግ በመንግሥት በኩል ጥረቶች እየተደረጉ ያለበት ሁኔታ እንዳለም ጠቅሰዋል። በተለይም በሌማት ትሩፋት ዓሳ እንደ አንድ የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ መታየቱ በጣም የሚበረታታ መሆኑን ገልጸው፣ በሌማት ትሩፋት መርሃግብሩ አዳዲስ ግድቦች ላይ የዓሳ ምርታማነት ለማሳደግ እየተደረገ ያለው ጥረት ይበል የሚያሰኝ መሆኑንም አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የተዳከሙትን ዳግም ለመጠገን እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ዘርፉ ወደ አንድ ደረጃ ከፍ እንዲል ያደርጉታል ተብሎ ይጠበቃል። ከዚሁ ጎን ለጎን የዓሳ ጫጩት ማባዣ ማዕከላትን በየክልሉ በማቋቋም ከፍተኛ እንቅስቃሴ እየተደረገ ሲሆን ኦሮሚያ ክልል በዝዋይ፣ ሲዳማ ክልል በሃዋሳ፣ በደቡብ ምዕራብ ክልል በአርባ ምንጭ የዓሳ ጫጩት ማባዣ ማዕከላት ተሰርተዋል።

እነዚህ ማዕከላት በሌማት ትሩፋቱና ከውጭ በተገኙ ፕሮጀክቶች ድጋፍ እየተከናወኑ መሆናቸውን ዶክተር ተስፋዬ ጠቁመው፤ ይሁንና እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የነበረው የዓሳ ጫጩት ማባዣም ሆነ እንደምርምር ማዕከል ያገለግል የነበረው ሰበታ የሚገኘው በኢንስትቲዩቱ ስር ያለው ብሔራዊ ዓሳ ምርምር ማዕከል ብቻ እንደነበር አንስተዋል። ይህ ማባዣ ማዕከል በዓመት እስከ አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን የሚደርሱ ጫጩቶችን እያባዛ ወደ ተለያዩ ግድቦችና ሰው ሰራሽ ኩሬዎች ይጨምር እንደነበርም ያስታወሳሉ። በእነዚህ ተቋማትም ሆኑ በክልሎች እየተሰሩ ያሉ የማባዣ ማዕከላት ስራ ሲጀምሩ የዓሳ ምርታቸው የተመናመነባቸውና አዳዲስ ግድቦች ላይ እየተባዙ ወደውሃ አካላቱ እንዲጨመሩ በማድረግ ዘርፉን በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ ጥረት እንደሚደረግ ያስገነዝባሉ።

**ኢትዮጵያ ካሏት የተፈጥሮ የውሃ አካላት ብቻ ከ128 እስከ 130 ሺ ቶን አሳ በዓመት ማምረት የሚያስችል አቅም አላት። የግብርና ሚኒስቴር ከሁለት ዓመት በፊት ባወጣው መረጃ እንደሃገር በዓመት እየተመረተ ያለው አሳ ግን ከ73 ሺ ቶን አይበልጥም፤ ይህም ያለንን ሃብት ሙሉውን መጠቀም አለመቻላችንን ያሳያል**

"ኢትዮጵያ 130 ሺ ቶን አሳ የማምረት አቅም አላት የሚባለው በተፈጥሮ ባሏት የውሃ አካላት ብቻ ነው እንጂ ሰው ሰራሽ ግድቦችን አይጨምርም" የሚሉት ዳይሬክተሩ፤ ግድቦችን ተጠቅሞ ደግሞ ከ400 ሺ ቶን በላይ አሳ ማምረት እንደሚቻል የግብርና ማስተር ፕላኑ እንደሚያሳይ ተናግረዋል።

ከሰው ሰራሽ ሃይቆችና ግድቦች አንፃር በአሁኑ ወቅት ተከዜ ላይ በጣም በርካታ ስራዎች መሰራታቸውን ጠቅሰው፤ ምርት የሚያመርቱባቸው ማስገሪያ መሳሪያዎች፣ የጀልባ፣ የመረብ፣ እንዲሁም ዓሳው ከተመረተ በኋላ ተቀናብሮ (ፕሮሰስ ተደርጎ) ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስችሉ የዓሳ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች ጭምር የተሟሉለት መሆኑን ያብራራሉ። በዚህ ረገድም በማህበራት በማደራጀት፤ ማህበራቱ እንዲጠናከሩ በማድረግ ሰፊ ስራ መሰራቱን አመልክተው፤ በአሁኑ ወቅት ምርቱ አዲስ አበባ ገበያ እየቀረበ ከፍተኛ ጥቅም እያስገኘ እንደሆነ ያስረዳሉ።

ከአባይ ግድብ ጋር ተያይዞ አሳ በስፋት ለማምረት በመንግሥት ታስቦ የነበረውን ስራ ተጠይቀውም ሲመልሱም "አባይ ግድብ ላይ ለመስራት የታቀደው የዓሳ ልማት ስራ በአሁኑ ወቅት በጅምር ደረጃ የሚጠቀስ ነው፤ ይሁንና ከፍተኛ የዓሳ ሃብት እንዳለ የሰራናቸው ጥናቶች ያሳያሉ" ብለዋል።

ኢንስትቲዩቱ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ባዘጋጀው ማስተር ፕላን መሰረትም ሰው ሰራሽ ሃይቅን በማስገር ብቻ በዓመት እስከ 10 ሺ ቶን ዓሳ ለማምረት የሚያስችል አቅም እንዳለው መታወቁን ያመለክታሉ። በተጨማሪ ደግሞ በዓሳ ግብርና ስራ ከተጠቀሰው ቁጥር በላይ በግድቡ ዙሪያ ማምረት እንደሚቻል ይናገራሉ።

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ በአባይ ግድብ ላይ በተሰራው ሰው ሰራሽ ሃይቅ ላይ ዓሳ ለማምረት ከ70 በላይ ማህበራት ፈቃድ የወሰዱ ሲሆን እስካሁን ወደ ስራ የገቡት ሶስት ማህበራት ብቻ ናቸው። በተጨማሪም ከአባይ ገድብ ጋር ተያይዞ መከላከያ ውስጥ ያለውና የሰራዊቱ ፋውንዴሽን አባላት ግድቡን እየጠበቁ በዓሳ ልማት ሥራ እንዲሰማሩ ታቅዷል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ 10 ሺ ሄክታር ተረክበዋል። ብሔራዊ ማዕከሉና ግብርና ሚኒስቴር በመተባበር ፋውንዴሽኑ ለሚያከናወነው የዓሳ ልማት የአዋጭነት ጥናት እያካሄዱ ይገኛሉ። ጥናቱ እንደተጠናቀቀም ወደ ማምረት ስራ ይገባሉ ተብሎ ይጠበቃል። አዋጭ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ የተወሰነ የዓሳ ምርት ወደ ውጭ የመላኩ እድል ይኖራል።

ይሁንና በተለይ በተፈጥሮ የውሃ አካላት ላይ እየተከናወነ ያለው የዓሳ ማስገር ሥራ ሥርዓት ሊበጅለትና አስገዳጅ ሕግ ወጥቶ ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ። ይህ ካልሆነ ሃብቱን ጥቅም ላይ ለማዋልም ሆነ ዘርፉ ለሃገር ኢኮኖሚ ወሳኝ ሚና እንዳይጫወት እንቅፋት ሆኖ ይቀጥላል የሚል ስጋት እንዳላቸው ዶክተር ተስፋዬ ይናገራሉ።

"አዳዲስና ሰው ሰራሽ ግድቦች ላይ ከሚከናወኑ የዓሳ ልማት ስራዎች ጎን ለጎን የዓሳና የውሃ አካላቱን ሕልውና መታደግ ቀዳሚ ስራ ሊሆን ይገባል። ከዚህ አንፃር የወጡ ሕጎችና ደንቦች ላይ በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች መከናወን ይኖርባቸዋል" ይላሉ። አስተማሪ የሆኑ እርምጃዎችንም በተጓዳኝ በመውሰድ ማስተማር ይጠበቃል። በተለይም እስከ ወረዳ ባሉ የመንግሥት መዋቅሮች ሕጎች በተጨባጭ መሬት ላይ እንዲተገበሩ መደረግ አለበት። የቁጥጥርና ክትትል ስራውም መከናወን ያለበት በታችኛው መዋቅር ላይ ባሉ አካላት መሆኑን ከግንዛቤ ማስገባት ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# መደበኛ ትምህርትን ለማጠናከር - የተጓዳኝ ትምህርት

**ግርማ መንግሥቴ**

ተጓዳኝ ትምህርት የመደበኛ ትምህርቱ አካል ነው የሚለው አያከራክርም። መደበኛ ትምህርቱም ያለ ተጓዳኝ ትምህርት ድጋፍ ልክ አይመጣም። በመሆኑም ሁለቱ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ የመሆናቸው ጉዳይ ለድርድር የሚቀርብ አይደለም። ችግሩ ሁለቱ ተነጣጥለው ከታዩና አንዱን የአንዱ ባዳ አድርጎ ማሰብና ማስላት ከተጀመረ ነው።

በተወሰኑ የትምህርት ዓይነቶች ክፍል ውስጥ በሚሰጥ ትምህርት ብቻ ብቁ የሆኑ ዜጎችን ማውጣት እንደማይቻል የሚያብራራው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የተጓዳኝ ትምህርት አደረጃጀት አፈፃፀም መመሪያ፣ (2007 ዓ.ም) እንደሚያስረዳው ከሆነ፣ "ተማሪዎች በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በኪነጥበብ፣ በስፖርት፣ በተፈጥሮና ማኅበራዊ ሳይንስ፤ እንዲሁም፣ በሌሎች ዘርፎች በንቃት በመሳተፍ ጊዜያቸውን በቁም ነገር ላይ ሊያሳልፉ ይገባል ይላል። ይህ ሲሆን የዕውቀት አድማሳቸው፣ ክህሎታቸውና አመለካከታቸው በሚፈለገው ደረጃ ይዳብራል። ከዚህ አንፃር የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራሞችን ከመደበኛው የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ጎን ለጎን በማደራጀት የተማሪዎችን ሁለንተናዊ እድገት ለማሟላት እንዲቻል እንደሌሎች አገሮች ሁሉ በኢትዮጵያም ዘመናዊ የትምህርት ስርዓት ከተጀመረ አንስቶ እንቅስቃሴዎች ሲካሄዱ ቆይተዋል። ይሁን እንጂ ሁሉም ትምህርት ቤቶች የተጓዳኝ ትምህርት አደረጃጀትን በመጠቀም በሚፈለገው መጠን ውጤታማ ስራዎችን ሰርተዋል ለማለት አያስደፍርም፡፡"

> **"የተጓዳኝ ትምህርት ከክፍል ውጭ በተማሪዎችና በመምህራን ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ ከመደበኛው የትምህርት ፕሮግራም ወይንም የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ውጭ ባለው ሰዓት የሚፈፀም ነው. . .**



ይኸው ሰነድ "የተጓዳኝ ትምህርት ከክፍል ውጭ በተማሪዎችና በመምህራን ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ ከመደበኛው የትምህርት ፕሮግራም ወይንም የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ውጭ ባለው ሰዓት የሚፈፀም ነው። የተጓዳኝ ትምህርት ትርጉም በእንግሊዝኛው ቋንቋ የተለያዩ ስያሜዎች የተሰጠው ሲሆን የተወሰኑ አገሮች 'co-curricular' ሲሉት ሌሎች ደግሞ 'Extra-class'፣ 'extra-curricular'፤ እንዲሁም 'Student Activities' ይሉታል፡፡" ካለ በኋላ "ቴክኖሎጂ እያደገ የአስተሳሰብ አድማስም እየሰፋ በመጣበት በአሁኑ ወቅት የሀገራችን የሥርዓተ ትምህርት ቀረጻ የተጓዳኝ ትምህርትን ያካተተና ከመደበኛው የመማር ማስተማር ሂደት በተጨማሪ እነዚህ ተግባራት የሚከናወኑበት የራሱ ጊዜ የተመደበ በመሆኑ የተጓዳኝ ትምህርትን ሊገልፅ የሚችለው የእንግሊዝኛ ቃል «co-curricular» የሚለው ገላጭ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡" በማለት ለጽንሰ ሀሳቡ ብያኔ ይሰጣል።

ይህ ሰነድ እንደሚለው "ስለተጓዳኝ ትምህርት ጠቀሜታ አሰራርና አፈፃፀም በቂ ግንዛቤ ያላቸው ትምህርት ቤቶች የተሻለ በመስራት ውጤት ለማስመዝገብ የቻሉ ሲሆን ሌሎች የተጓዳኝ ትምህርት አደረጃጀት አሰራርና አፈፃፀም በተገቢው ግንዛቤው የሌላቸው ግን በሚፈለገው ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ" አልቻሉም።

"'Co-curricular' የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል በሀገራችን 'የተጓዳኝ ትምህርት' የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን፣ ይህም ከክፍል ውስጥ ትምህርት ውጭ በመደበኛው የትምህርት አሰጣጥና ስልት መሠረት ከሚፈፀሙ ተግባራት በተጨማሪ የተማሪዎችን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡" በመሆኑም በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን ተማሪዎችን እንደ ዝንባሌያቸው በማስተባበርና የተጓዳኝ ትምህርትን በመምራት በተማሪዎች ዘንድ የሚፈለገውን የባህሪ ለውጥ እንዲፈጠር ለማድረግና ተማሪዎች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ በትምህርት ቤቶች የማመቻቸቱ ተግባር የመምህራን ይሆናል።

የተጓዳኝ ትምህርት "የተዘጋጀውን ሥርዓተ ትምህርት ተማሪዎች የበለጠ እንዲረዱትና ወደ ተግባር እንዲለውጡት" ያስችላቸዋል የሚለው ሰነድ "የተጓዳኝ ትምህርት አደረጃጀት፣ አመጣጥ፣ አሠራርና ጠቀሜታ በተለያዩ አጋጣሚዎችና ሰነዶች ሲገለጽና ሲቃኝ የኖረ ነው። ሆኖም በሀገራችን ብሎም በአዲስ አበባ የሚጠበቀውን ያህል ስኬታማ ነው ለማለት ያዳግታል፡፡" ሲልም የላይኛውን ሀሳቡን የሚያጠናክር ሲሆን፤ ያለውን እጥረትና ክፍተትም:-

- አደረጃጀታቸውም ሆነ አፈፃፀማቸው በእውቀት፣ በተጠያቂነትና በአሳታፊ መዋቅር ላይ የተመሠረተ ነው ለማለት ያዳግታል፤
- በእቅድ የተያዘና በመርሀ ግብር የታገዘ የአፈፃፀም፣ የክትትልና ድጋፍ ከፍተኛ እጥረት ይታይበታል፤
- የተደራጀ ወቅታዊ ተገቢ የመረጃ አያያዝ ችግር ይንፀባረቃል፤ በአደረጃጀት፣ በአተገባበርና በተጨበጠ ስኬት ላይ የተመሠረተ የማትጊያ የእውቅና መስጫ ጠንካራ ሥርዓት የለውም፤
- የግብዓት እጥረት፣ በጀት አለመመደቡና በፍትሃዊነት ያለመጠቀም ችግሮች ይታያሉ፤
- ከባለድርሻ አካላት ጋር ተገቢ የሆነና ዘላቂነት ያለው የትስስርና የመዋቅር ግንኙነት ክፍተት አለበት፤
- የተጓዳኝ ትምህርት አደረጃጀትና አተገባበርን በየጊዜው ከሚስተዋለው የሣይንስና የቴክኖሎጂ እድገትና ለውጥ ጋር እየፈተሹ፣ እያሻሻሉና እያደራጁ አለመጓዝ ወዘተ ቁልፍ አመላካች እጥረቶች በየጊዜው ይስተዋላሉ፡፡

በማለት ይዘረዝራል። እነዚህን ችግሮች "ለመፍታት በቢሮ ደረጃ አንድ ወጥና ግልፅ የሆነ ማንዋል ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡"

"በመሆኑም ቀደም ሲል በ1989 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀውን የተጓዳኝ ትምህርት የአፈፃፀም መምሪያ (ማኑዋል) መነሻ በማድረግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የሚመራቸው የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ትምህርት ቤቶች እንዲጠቀሙበትና ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደት ለመፍጠር እንዲችሉ" አንድ ራሱን የቻለ የአፈፃፀም መምሪያ ማዘጋጀቱን ትምህርት ቢሮው አስታውቋል። የመምሪያውን ዓላማም:-

- ከትምህርት ቢሮ እስከ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ አመራሮች አደረጃጀቱን፣ አሰራሩንና አፈጻጸሙን በዕውቀት ለመምራት እንዲችሉ አቅም መፍጠር፤
- በተጓዳኝ ትምህርት አደረጃጀቶች ተሳትፎ የሚያደርጉና ቀጥታ የሚመለከታቸው መምህራንና ተማሪዎች መምሪያውን እየተጠቀሙ ዕቅድን፤ መረጃን፣ ሂደትንና ውጤትን መሠረት ያደረገ ስራ እንዲሰሩ ማስቻል፤
- ተማሪዎች የሥራ የአመራር ባህልንና የተለያዩ ክህሎቶችን አዳብረው ዝግጁ በመሆን ለህብረተሰቡ ጠቀሜታ ሊሰጡ በሚችሉ ስራዎች ላይ በቂ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማድረግ፤

በማለት ዘርዝሯል።

የትምህርቱን ቅርፅና ይዘት አስመልክቶ ባሰፈራቸው አንቀፆች ስር የትምህርቱን መነሻ በተመለከተም:-

"የተጓዳኝ ትምህርት ምንጭ ከማህበራዊ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ተፈጥሮ ሳይንስ፣ ባህልና ስነጥበብ፣ ስፖርትና ቱሪዝም ወዘተ... የተገኘ ነው። መሠረታዊ ሀሳቡ በክፍል ውስጥ ሊሰጥ ከተዘጋጀውና ከዚያም ውጭ ባሉ ማህበረሰባዊ ጉዳዮች የሚወሰድ በመሆኑ ወደ ተግባር የሚለወጥና ጠቀሜታ ያለው አሰራር ሲሆን በማንኛውም የትምህርት ቤት ደረጃና የመማር ማስተማር ስራ አጋዥ እንቅስቃሴ ነው።

"ትምህርት ቤቶች እንደ ራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ስርዓተ ትምህርቱን ወደ ተግባር ይለውጡታል ተብሎ የሚታመንባቸውን ጉዳዮች በመለየት በተጓዳኝ ትምህርት አደረጃጀቶች እንዲታቀፉ ያደርጋሉ። አደረጃጀቱ ለአመራር እንዲመችና የነበረውን የክበባት ያለ ልክ መለጠጥ ለማስቀረት በትምህርት ቤት ደረጃ የተጓዳኝ ትምህርት አደረጃጀት ቅርፅ በዚህ መምሪያ (ማንዋል) ላይ ለማስቀመጥ ተሞክሯል። በየአደረጃጀቱ ስር ተያያዥነት ያላቸው ተጨማሪ ተግባራትንና ክበባትን ማዋቀር የሚቻል ሲሆን በመምሪያው የቀረበው መነሻ ሃሳብ መሆኑም ሊታወቅ ይገባል፡፡" ሲል አስፋፍቶ ይገልፀዋል።

መመሪያው የተጓዳኝ ትምህርት የሚደራጅበት ዓላማ ከአጠቃላይ ትምህርት ማሕቀፉ ፋይዳ ተነጥሎ የሚታይ ባለመሆኑ በተገቢው መንገድ የተደራጀና ተግባር ውስጥ የገባ አደረጃጀት(ቶች) የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተሉት መሆናቸው ይዘረዝራል።

1. በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን የንድፍ ሃሳብ ትምህርት በተግባር መረዳት እንዲችሉ በማድረግ የግልና የማህበራዊ ዕድገትን ያፋጥናል፤
2. የሰብዓዊ ግንኙነት ክህሎትን በማዳበር ሌሎችንም የማክበርና የመከባበር ስርዓትን ይማሩበታል፤
3. ራስን የመግለፅ፣ ከሰዎች ጋር የመወያየት፣ የማመንና የማሳመን፣ የማወቅና የማሳወቅ፣ የውይይት ስነስርዓቶችን የማወቅ፣ ውሣኔ የመስጠትንና በውይይት የመተማመንን ሂደት፤ እንዲሁም፣ አመራርን፣ ኃላፊነትን፣ ተጠያቂነትን ሁሉ እንዲማሩበትና እንዲለማመዱት ያግዛል፤
4. የመቻቻል ባህልን በማዳበር ቅራኔዎችን በውይይት የመፍታትን ሕግና ደንብ ስርዓት እንዲማሩበት ያግዛል፤
5. ለሥራ አክብሮት መስጠትን፣ የጊዜን ጠቀሜታ መረዳትን፣ ሥራ ማህበራዊ መሆኑን የመገንዘብና የቡድን ሥራን እንዲለማመዱ ይረዳል፤
6. የፈጠራ ችሎታ በማሳደግ ለቴክኖሎጂ ዕድገት መሠረት የሚጥሉ የተማሪዎች ልዩ ልዩ ፈጠራዎችና ተሰጥዖ እንዲጎለብት ያደርጋል፤
7. በትምህርት አቀባበላቸው ደከም ያሉ ተማሪዎች እንዲታገዙበት ያደርጋል፤
8. የትምህርት ቤቱንና የህብረተሰቡን ግንኙነት ይበልጥ ያጠናክራል፤
9. የወደፊት ሥራንና ሙያን የማስተዋወቅ ጠቀሜታ አለው፤
10. አካባቢያዊ፣ ክልላዊ፣ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ የሆኑ ጉዳዮችንና አዳዲስ ክስተቶችን፤ እንዲሁም፣ ችግሮችንና ግኝቶችን የማስተዋወቅ ጠቀሜታ አለው፤
11. ጤናማ ዜጋ በትምህርት ቤቶች ለማፍራት ያስችላል፤
12. በስነምግባራቸው የበቁ የተሻለ ውጤት ባለቤት ሊሆኑ የሚችሉ ተማሪዎችን ኮትኩቶ ለሀገር ዕድገት፣ ለዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታና ለመልካም አስተዳደር መስፈን አስተዋፅዖ ሊያደርጉ የሚችሉ ዜጐችን ማፍራት ያስችላል።

ከዚህ በላይ ሰፋ አድርገን የሄድንበትን ተጓዳኝ ትምህርት መሬት ላይ፣ በየትምህርት ተቋማቱ ያለው ወቅታዊ ይዞታ ምን ይመስላል? የሚለውን ለማወቅ በተወሰኑና ይወክሉልናል ባልናቸው የትምህርት ተቋማት ተዘዋውረን ለመመልከት ሞክረናል። በዚሁ ሙከራችንም የተለያዩ የክበባት እንቅስቃሴዎች መኖራቸውን አይተናል።

የአራት ኪሎው የዳግማዊ ምኒልክ ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛ ደረጃ፣ መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከተመለከትናቸው ትምህርት ቤቶች አንዱ ነው።

በዚሁ ትምህርት ቤት ተገኝተን እንደ ተመለከትነው በተቋሙ ውስጥ 21 ክበባት ያሉ ሲሆን፣ ተማሪዎች እንደየ ፍላጎታቸውና ዝንባሌያቸው በክበባቱ ይሳተፋሉ፤ በአንድም ይሁን በሌላ የማይሳተፍ ተማሪ የለም።

ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ቀርበን መረዳት እንደ ቻልነው እነዚህ 21 ክበባት በሙሉ ከላይ (ከትምህርት ቢሮ) የወረዱ ሲሆን፤ ወጥ በሆነ መልኩ በከተማ መስተዳድሩ ስር በሚገኙ፣ በሁሉም ትምህርት ተቋማት እየተተገበሩ ይገኛሉ።

ስማቸው እንዳይገለጽ ምስላቸውም እንዳይታይ የነገሩንና መረጃውን የሰጡን ምንጮች እንደነገሩን፤ ወቅቱን ያገናዘቡና ተጨባጭ ሁኔታዎችን ሊያሰርፁ የሚችሉ ክበባት በተጓዳኝ ትምህርት ስር ተካተዋል። ይህም ተጓዳኝ ክበብን ከወትሮው የተለየ አድርጎታል። የክበባቱ ውቅር በአቀራረባቸው ከሕይወት ጋር የተቆራኙ፣ በርካታ ተግባራትን ያቀፉ ጭብጦች ያሏቸው፣ ከተለያዩ የትምህርት መስኮች ጋር የተገናኙ ዕውቀት፣ ግንዛቤና ክህሎቶችን ያዋህዱና ተማሪዎች በተሻለ ጥራት እውቀት እንዲገበዩ የሚያስችሉ ሆነው የተደራጁ ናቸው ማለት ይቻላል።

ካገኘነው መረጃ መረዳት እንደቻልነው፣ ባህል እና ኪነጥበብ፣ የመንገድ ደህንነት፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ፣ የግብርናና የእንስሳት ርባታ፤ የእጅ ስራ፣ የአካባቢ እንክብካቤ፣ ሥነ-ምግብ፣ ፀረ-ሙስና፣ ግብረ-ገብ፣ የመማክርት ክበብ ወዘተ እና የመሳሰሉት የተጓዳኝ ክበባትን ከድሮዎቹ ለየት፣ ሰፋና በርከት ያሉ ይሆኑ ዘንድ አድርገዋቸዋል።

በአጠቃላይ፣ የትምህርት ተቋማት ከቀለም እውቀት ባሻገር ተማሪዎች በርካታ ግንዛቤዎች የሚጨበጡባቸው፤ የተለያዩ ክህሎቶች የሚዳብሩባቸው፤ ጠንካራ ማህበራዊ ሕይወት የሚመሰረትባቸው፤ ክፉና ደጉን የሚለዩባቸው፤ የወደፊት ሕይወታቸውን መሰረት የሚጥሉባቸው፤ በርካታ መልካም ትዝታዎችን ከወዲሁ የሚሰንቁባቸው፤ የአኗኗር፣ የአመራር፣ የአሰራር ወዘተ ብቃታቸውን የሚያጎለብቱባቸው፤ ኃላፊነቶችን መሸከምና መወጣትን ከወዲሁ የሚለማመዱባቸው፤ ከሁሉም በላይ ዝንባሌና ፍላጎታቸውን በመገንዘብ የወደፊታቸውን ከወዲሁ የሚያማትሩባቸው ልዩ ስፍራዎች ናቸው። ከእነዚህ አንዱ ደግሞ ተጓዳኝ ትምህርት ነው። በመሆኑም፣ ሁሉን አቀፍ በሆነና በተሟላ መልኩ ተደራጅተው ብቁ ዜጋ ማፍራቱ ላይ ሊዘናጉ አይገባም።

# “እንደ ተቋም በኮሪደር ልማቱ ዘላቂ ተጠቃሚነትን አግኝተናል”

- አቶ መላኩ ታዬ

የአገልግሎቱ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር

ራስወርቅ ሙሉጌታ

**በኢትዮጵያ ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ቢመጣም ዛሬም ድረስ በርካታ ዜጎች ለመብራት አገልግሎት የሚውል ኃይል እንኳን እያገኙ አይደለም፡፡ በተመሳሳይ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራቱንም በለውጥ መንገድ ላይ መሆኑ በተደጋጋሚ ቢነገርም ዛሬም ድረስ ከተጠቃሚዎች የሚነሱ በርካታ ቅሬታዎች መኖራቸው ይታወቃል። እኛም ለዛሬው ዝግጅታችን ለእነዚህ ጥያቄዎች የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ መላኩ ታዬ የሰጧቸውን ምላሾች እንደሚከተለው አዘጋጅተን አቅርበነዋል።**

**አዲስ ዘመን፡- አገልግሎቱ ተደራሽነትን ከማረጋገጥ አኳያና ራሱን በማደራጀት ረገድ ሲሰራቸው የነበሩ ተግባራት እንዴት ይገለጻሉ ?**

**አቶ መላኩ፡-** የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ሁለንታናዊ ለውጥ በማስመዝገብ ላይ ይገኛል። የቅርብ ጊዜውን እንኳን ብንመለከት ያለፉት አራት ወራት ከመቼውም ጊዜ የላቀ ውጤት የተመዘገበባቸው ነበሩ ማለት ይቻላል። አገልግሎቱ ራሱን ለማሻሻል ከሚሰራቸው ቀዳሚ ስራዎች መካከል በሰው ኃይልና እና በግብአት ራሱን ለማደራጀት አንዲችል በቂ ገቢ መሰብሰብ ነው። በዚህም ረገድ አገልግሎቱ በ2017 ዓ.ም በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ከኢነርጂ ሽያጭ፣ ከአዲስ ደንበኞች መስተንግዶ፣ ከማያገለግሉ ንብረቶች ሽያጭ እና ከሌሎች ልዩ ልዩ የገቢ ምንጮች በአጠቃላይ 11 ነጥብ 55 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 11 ነጥብ አስራ 15 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ አመርቂ አፈፃፀም ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

በተጨማሪ ከኢነርጂ ሽያጭም ብር ስምንት ነጥብ 26 ቢሊየን ለመሰብሰብ ታቅዶ ስምንት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ይህም ባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተሰበሰበው ስድስት ነጥብ 21 ቢሊዮን ብር ጋር ሲነጻጸር የ32 ነጥብ አንድ በመቶ ብልጫ አለው፡፡ ከአዲስ ደንበኞች አገልግሎት ከተገኘ ገቢም ሁለት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር፥ እንዲሁም የማያገለግሉ ንብረቶችን በማስወገድና ከልዩ ልዩ የተገኘ ገቢ አፈፃፀም 183 ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ብር ነው፡፡ ይህ ገንዘብ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጻር 41 ነጥብ አራት በመቶ ብልጫ አሳይቷል። ምንም እንኳን ይህ አሃዝ አገልግሎቱ ሊደርስበት ከሚገባውና አጠቃላይ እቅዱና እንደ ሀገር ከሚጠበቀው ለውጥ አንጻር ብዙ የሚቀረው ቢሆንም በተስተካከለ መንገድ ላይ መሆኑን ግን የሚያመላክት ነው።

ሌላው አገልግሎቱ እንደ እቅድ እየሰራባቸው ካሉ ጉዳዮች መካከል የተደራሽነት አድማሱን ማስፋት ነው። በዚህ ረገድ በሩብ ዓመቱ 120 ሺህ አዳዲስ ደንበኞችን የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ከ90 ሺህ 726 በላይ አዳዲስ ደንበኞችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። በ2015 ዓ.ም ተመሳሳይ ወቅት 46 ሺህ 713 አዳዲስ ደንበኞችን ነበር የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለው። አጠቃላይ የተቋሙን የደንበኛ ቁጥር ወደ አራት ሚሊዮን 850 ሺህ 800 ለማሳደግ በቅቷል። ባለፉት ሦስት ወራት ሰፊ የቅድመ መከላከል ጥገና፣ የአስቸኳይ ጥገና፣ የማሻሻያና መልሶ ግንባታ ሥራዎች ተከናውነዋል። አዲስ 31 የገጠር ቀበሌዎችን ከዋናው ቋት (ግሪድ) በማገናኘት የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 26 የገጠር ቀበሌዎችን ለማገናኘት ተችሏል። በዚህ ሁሉ ሂደት ለሦስት ሺህ 376 ዜጎች አዳዲስ የሥራ ዕድል ለመፍጠርም ተችሏል።

እነዚህንስራዎችለማከናወንእናከላይየተጠቀሰውን ውጤት ለማስገኘት የአገልግሎቱ ሰራተኞች በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሆነው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛል። የሰሜኑ ጦርነት ከተካሄደ በኋላ በትግራይ መልሶ ግንባታ እግር በእግር እየተከታተለ በማካሄድ ሕዝቡን ተጠቃሚ ለማድረግ የተሰሩ ስራዎች ለዚህ እንደ አብነት ይጠቀሳሉ። በቅርቡም በምእራብ ኦሮሚያ በወለጋ እና አካባቢው ለዓመታት ያለ ኤሌክትሪክ የቆዩ ከ150 በላይ አካባቢዎችን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለማድረግ የተሰሩ ስራዎች እና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል። ለዚህ ውጤት ተቋሙም እንደ አሰራር ሰራተኞቹም እንደ አንድ ግለሰብ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥም በመሆን የሕዝብን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ብዙ ተሰርቷል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሰራተኞች የአደጋ መከላከያ ቁሳቁስ በማቅረብና በእንቅስቀሴ ወቅት ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ የተካሄዱ ስልጠናዎችም ውጤታማ በመሆናቸው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለጉዳት የሚዳረጉ ሰራተኞችን ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ተችሏል። በሶስተኛ ወገን በሕብረተሰቡ ላይ እየደረሱ ያሉ አደጋዎች ግን ዛሬም ትኩረት የሚፈልጉ ናቸው። በተለይም ከቆጣሪ ውጪ ወደ ቤት በሚገባ መስመር በሚፈጠር ንክኪ በሚደረስ አደጋ። እንዲሁም ከአንድ ግለሰብ ወደሌላ ሰው ቤት በሕገወጥ መንገድ ደረጃውን ባልጠበቀ ገመድ ኤሌክትሪክ በመውሰድና በቤት ውስጥ የኤሌክትሪክ እቃዎች ጋር በተያያዘ የሚደርሱ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚሰሩ ስራዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን ፡- አገልግሎቱ ለሕብረተሰቡ የሚሰጠውን አገልግሎት በማቀላጠፍ እና ዘመናዊ በማድረግ ረገድ ምን ምን ስራዎችን አከናውኗል ?**

**አቶ መላኩ፡-** በሩብ ዓመቱ የተለያዩ የክፍያ አማራጮችን በማስፋፋት በተለይ የዲጂታል ክፍያ አማራጮችን የሚጠቀሙ ደንበኞች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል። በአሁኑ ወቅት ከድህረ ክፍያ ተጠቃሚ ደንበኞች ውስጥ ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆኑት ወርሃዊ የፍጆታ ክፍያቸውን እያከናወኑ ያሉት በዲጂታል የክፍያ አማራጭ ነው። በዚህም ከሁለትና ከሶስት ዓመታት በፊት በየቦታው ይታይ የነበረውንና በብዙዎች ዘንድ ቅሬታ ሲቀርብበት የነበረውን ረዥም ሰልፍ ማስቀረት ችለናል። የቅድመ ክፍያ አገልግሎት ተጠቃሚ በተጨማሪም ደንበኞችም ወደ አገልግሎት መስጫ ተቋማት በመቅረብ ኃይል መሙላት ሳያስፈልጋቸው ቤታቸው ሆነው በኦንላይን የሚከፍሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ያሉ ሲሆን በዚህ ዓመት ይጠናቀቃሉ ተብሎ ይታሰባል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ባለፉት ሶስት ወራት ብቻ 120 ሺህ አዳዲስ ደንበኞች 62 በመቶ የሚሆኑት በተቀመጠው የጊዜ እቅድ መሰረት ኤሌክትሪክ አገልገሎት ለማግኘት በጠየቁ በአስር ቀናት ውስጥ ቆጣሪ እንዲገባላቸው ማድረግ ተችሏል። በቅርቡ ደግሞ «አንድ ቀን የኤሌክትሪክ ዘመቻ የሚል » በማካሄድ በተለያዩ ቦታዎች ጥያቄው በቀረበበት ቀን ቆጣሪ እንዲያገኙ እየተደረገም ይገኛል። ይህ አሰራር ዛሬም ድረስ እየተተገበረ ያለና ለብዙዎች እፎይታ የሰጠም ነው።

ይህም ሆኖ አገልግሎቱ ውድ እንደመሆኑ ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ መሆኑ ግልጽ ነው። በዚህም ከአዲስ አገልግሎት ፈላጊ ጋር እና ከአስቸኳይ ጥገና ጋር በተያያዘ የሚታያዩ በርካታ ክፍተቶች ነበሩ። ይህንን በዘላቂነት ለመፍታት ቀዳሚው መንገድ ቴክኖሎጂ መጠቀም ነው። ይህም አገልግሎት ጥያቄ የማቅረቡን ሂደት እና ቅሬታ የማቅረብንም አካሄድ የሚመለከት ይሆናል። ይህም ሆኖ በማንኛውም ጊዜ በሙስና እና በብልሹ አሰራር የሚገኙ የተቋሙ ሰራተኞች ላይ ተገቢውና አስተማሪ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል፡፡ ይህ በቀጣይም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- መንግስት ያደረገው የታሪፍ ማሻሻያ በጣም የተጋነነ ከመሆኑ በተጨማሪ ወቅቱን ያላገናዘበና የዜጎችንም አቅም ከግምት ያላስገባ ነው ይባላል። የታሪፍ ማስተካከያ ለማድረግ ሲወሰን በአገልግሎቱ በኩል ምን ጥናት ተካሂዶ ነው?**

**አቶ መላኩ፡-** የታሪፍ ማሻሻያው በኢነርጂ መመሪያው መሰረት በየአራት ዓመቱ ተግባራዊ የሚደረግ ነው። ነገር ግን የዛሬ ሁለት ዓመት ማሻሻያው ባለመደረጉ አሁን እየተተገበረ ያለው ከስድስት ዓመት በኋላ መሆኑ መታወቅ አለበት። ላለፉት ሁለት ዓመታት

ወደ ገጽ 10 ዞሯል



“በአሁኑ ወቅት ከድህረ ክፍያ ተጠቃሚ ደንበኞች ውስጥ ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆኑት ወርሃዊ የፍጆታ ክፍያቸውን እያከናወኑ ያሉት በዲጂታል የክፍያ አማራጭ ነው

# ወቅታዊ

# “እንደ ተቋም በኮሪደር ልማቱ ዘላቂ...

ከገጽ 9 የዞረ

ተገልጋዩ ክፍያ ሲፈጽም የነበረው ማሻሻያ ሳይደረግ ቀድሞ በነበረው ነው። ባለፈው አንድ ዓመት ውስጥ ግን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የተውጣጡ ባለሙያዎች ረዘም ያለ ዝርዝር ጥናት ሲያካሂዱ ቆይተዋል። በተጨማሪም ተመሳሳይ ጥናት በሶስተኛ ወገን እንዲካሄድ ተደርጓል። ይህንን ጥናት መሰረት በማድረግ የአገልግሎቱ ተቆጣጣሪ የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን ጥናቱን መርምሮ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ የጸደቀ ታሪፍ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

ምንም እንኳን ታሪፉ የጸደቀው ከ2016 ዓ.ም ከሰኔ ወር በፊት ቢሆንም ተግባራዊ የሚደረገው ከዘንድሮ መስከረም አንድ ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ነው። ጥናቱ የተካሄደው በአሁኑ ወቅት እየተካሄደ ካለው ሀገራዊ ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ሪፎርምም በፊት የተጠናቀቀ ነው። ጥናቱ ሲካሄድ ከግምት አስገብቶ መረጃ ሲሰበስብባቸው ከነበሩ ጉዳዮች መካከል አንዱ የኅብረተሰቡ የመክፈል አቅም ነበር። በዚህም የአገልግሎቱ 65 በመቶ የሚሆነው ደንበኛ ከ50 ኪሎ ዋት በታች የሚጠቀም ነው። እነዚህ የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚጠቀሙት የኃይል መጠን በጣም ዝቅተኛ ሲሆን፣ ከአጠቃለይ ኃይል ስምንት በመቶ ብቻ የሚወስድ ነው። በዚህም መነሻ ከዜሮ እስከ ሀምሳ ኪሎ ዋት የሚጠቀሙ ደንበኞች የ75 በመቶ የታሪፍ ማሻሻያ ድጎማ ተጠቃሚ ናቸው።

በተመሳሳይ ከ51 እስከ አንድ መቶ ኪሎ ዋት የሚጠቀሙ ደንበኞች 40 በመቶ የታሪፍ ማሻሻያ ድጎማ ተጠቃሚ ናቸው። እንዲህ እያለ ሄዶ እስከ 300 ኪሎ ዋት የሚጠቀሙት ደግሞ አራት በመቶ የታሪፍ ማሻሻያ ድጎማ ተጠቃሚ ይሆናሉ። ከዚህ በላይ ኃይል ተጠቃሚ ደንበኞች በመጀመሪያ ደረጃ በቁጥር በጣም ትንሽ ሲሆኑ፣ በሁለተኛ ደረጃ ከፍተኛ ኃይል የሚጠቀሙ በመሆኑ ከፍተኛ ገቢ ያገኛል ተብሎ ይታሰባል። በመሆኑም በእነዚህ ላይ ታሪፉ ሙሉ ለሙሉ የሚተገበር ይሆናል።

ይህም ሆኖ ከዚህ በፊት የታሪፍ ማሻሻያዎች ተግባራዊ ሲደረጉ ምንም እንኳን በየአራት ዓመቱ የሚደረጉ ቢሆንም ከጸደቁበት ጊዜ አንስቶ ጭማሪውን በሙሉ ተገልጋዩ እንዲከፍል ይደረግ ነበር። በአሁኑ ዓመት ግን ከቀደመው በተለየ አካሄድ የማኅበረሰቡን የመክፈል አቅም ከግምት በማስገባት የሚኖርበትን ጫና ለመቀነስ ክፍያው በየሩብ ዓመቱ እየተሻሻለ እንዲሄድ ተደርጓል። ይህም ማለት በጥናቱ የተወሰነውና የጸደቀው የገንዘብ መጠን ሙሉ ለሙሉ የሚተገበረው የዛሬ ዓመት ይሆናል ማለት ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በዋናነት ሊታወቅ የሚገባው መሰረታዊ ጉዳይ የታሪፍ ማሻሻያ ለምን ይደረጋል የሚለው ነው።

ይህንን ስንመለከት ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የምንጠቀምባቸው መሰረተ ልማቶችን ለመገንባት የሚውሉ ግብአቶች ከሰባ በመቶ በላይ ከሌሎች ሀገራት በውጪ ምንዛሬ የሚገባ ነው። እነዚህ ግብአቶች ከዓለም ገበያ የሚሸመቱ በመሆናቸው ከፍተኛ ገንዘብ የሚያስፈልግ ይሆናል። ማለትም አገልግሎቱ በትንሹ በየወቅቱ የሚያወጣውን ወጪ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን እየሸፈነ መቀጠል ይኖርበታል። ይህ የሚደረገውም በአንድ ወገን አገልግሎቱ አሁን እየሰጠ ያለውን አገልግሎት እንዳያቋርጥ ወይንም እንዳይቀንስ ሲሆን፤ በሌላ በኩል በየወቅቱ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ፍላጎት የሚቀርብ በመሆኑ እነዚያን ዜጎች ተደራሽ ለማድረግ ኃላፊነትም ስላለበት ነው።

በተጨማሪ ሁሉም ደንበኞች ሊባል በሚያስደፍር መልኩ ዘመኑ የደረሰበትን የተሻሻለ ዘመናዊ አገልግሎት ማግኘት ይፈልጋሉ። ወቅቱን የሕዝብ ጥያቄ ለመመለስ በየከተማው የመልሶ ግንባታና የኔትወርክ ማሻሻያ ስራዎች በመከናወን ላይ ናቸው። እንደ ሀገር በአሁኑ ወቅት የኤሌክትሪክ ተጠቃሚው ሕዝብ ቁጥር እንደ ሀገር ከ54 በመቶ የዘለለ አይደለም። ይህ ማለት አገልግሎቱ ቀሪውን 46 በመቶ ዜጎች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ የማድረግ ኃላፊነት ይጠበቅበታል ማለት ነው። እነዚህ ከላይ ያነሳናቸው ዝርዝሮች እንደሚያመለክቱት የታሪፍ ማሻሻያው ጊዜውን ያማከለ፣ ተመጣጣኝ እና የተሻለ አገልግሎት ለኅብረተሰቡ ለመስጠት ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ነው።



**አዲስ ዘመን፡- እንደ ሀገር እየተካሄደ ባለው የኮሪደር ልማት በርካታ ቤቶች ሲነሱ የኤሌክትሪክ መቋረጥ እንደተከሰተ ይታወቃል። ይህን ተከትሎ የፍጆታ ክፍያና የአገልግሎቱን ሀብቶች በመሰብሰብ ረገድ ምን ምን ተግባራትን አከናውናችኋል ?**

**አቶ መሳኩ ፡-**የኮሪደር ልማቱን ተከትሎ ከአገልግሎቱ በርካታ ስራዎች ይጠበቁ እንደነበር እናውቃለን። በዚህም መሰረት ከተጀመረ አንስቶ ከሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራን እንገኛለን። በእያንዳንዱ የኮሪደር ልማት አስተባባሪ ኮሚቴ ውስጥም የአገልግሎቱ ተወካዮች እንዲኖሩ ተደርጓል። በመጀመሪያው ዙር የአዲስ አበባ የኮሪደር ልማት 24 ሰዓት ስንሰራ ነበር። ከኮሪደር ልማቱ በፊት የነበሩን ኔትወርኮች በጣም አስቸጋሪ የነበሩ እንደ ሸረሪት ድር እርስ በእርስ የተጠላለፉና ለአደጋና ለኃይል መቆራረጥ ምቹ የሆኑ ነበሩ። በአሁኑ ወቅት ግን የኮሪደር ልማቱ በተከናወነባቸው ቦታዎች በሙሉ መስመሮች ደረጃቸውን በጠበቀ ሁኔታ በመሬት ውስጥ እንዲገነቡ ለማድረግ ተችሏል። በኮሪደር ልማቱ በተነሱ ሰፈሮች የነበሩ ቤቶች ላይ ካሉ ቆጣሪዎች ከመነሳታቸው በፊት በባለሙያዎች የተጠቀሙትን ንባብ ወስደናል።

በዚህም ክፍያ ያለበት እንዲከፍል እየተደረገ ቆጣሪው ወደተቋሙ እንዲለመለስ ተደርጓል። ሌላ ቦታ ሲገቡ አዲስ የኃይል መስመር የሚዘረጋላቸውም የመጀመሪያውን አገልግሎት ማጠናቀቃቸውን የሚገልጽ ማረጋገጫ ሲያቀርቡ ነው። አሁንም ሁለተኛውን ዙር በአዲስ አበባም ሆነ በክልሎች በየሳምንቱ እየተከታተልን እየገመገምን እየሰራንበት ይገኛል። የኮሪደር ልማቱ ከግብአት እጥረት አንጻር የገጠሙ ክፍተቶች ቢኖሩም እንዳጠቃላይ ለአገልግሎቱ ብዙ ትምህርቶችንም የሰጠ ነው ለማለት ያስደፍራል። ከዚህ ቀደም ዓመታት ይወስዱ የነበሩ ስራዎችን ቀን ከሌሊት በመስራት በአጭር ጊዜ ማጠናቀቅ የሚያስችለን ብቃት አግኝተንበታል። የስራ ባህላችንንም ፈትሸን እንድንቀይር ያስቻለም ነው። በዚህም እንደ ተቋም በኮሪደር ልማቱ ዘላቂ ተጠቃሚነትን አግኝተናል ለማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን ፡- አገልግሎቱን በተመለከተ በተደጋጋሚና በስፋት ከሚነሱ ቅሬታዎች መካከል የኃይል መቆራረጥ ይነሳል። እንዲያውም በአንዳንድ አካባቢዎች ፈረቃ ከተጀመረ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ለምን በግልጽ አይነገረንም እስከማለት የተደረሰበት ሁኔታ በዚህ ረገድ ምን ስራ እየተከናወነ ይገኛል ?**

**አቶ መሳኩ፡-** የኃይል መቆራረጥ ችግር በአንዳንድ

**ከኮሪደር ልማቱ በፊት የነበሩን ኔትወርኮች በጣም አስቸጋሪ የነበሩ እንደ ሸረሪት ድር እርስ በእርስ የተጠላለፉና ለአደጋና ለሀይል መቆራረጥ ምቹ የሆኑ ነበሩ። በአሁኑ ወቅት ግን የኮሪደር ልማቱ በተከናወነባቸው ቦታዎች በሙሉ መስመሮች ደረጃቸውን በጠበቀ ሁኔታ በመሬት ውስጥ እንዲገነቡ ለማድረግ ተችሏል**

አካባቢዎች መኖሩን እናውቃለን። በፈረቃ አገልግሎት እየተሰጠ እንዳልሆነ ግን ሁሉም ዜጋ ሊያውቅ ይገባል። የኃይል መቆራረጥ እንኳን እንደ ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ባሉና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ያልተደገፈ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ማቅረቢያ መሰረተ ልማት ባላቸው ሀገራት ይቅርና ባደጉትም ሀገራት የሚከሰት ነው። የኃይል መቆራረጥን ሙሉ ለሙሉ ማስቀረት ባይቻልም መቀነስ ግን እንደሚቻል ግልጽ ነው። በኢትዮጵያ እየተከሰተ ያለው የኃይል መቆራረጥ የመጀመሪያው ምክንያት መሰረተ ልማቶቹ ለረዥም ዓመት አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩና ያረጁ በመሆናቸው ነው። እነዚህ መሰረተ ልማቶች ዛሬ ያለውን ተገልጋይ ታሳቢ አድርገው የተገነቡ ባለመሆናቸው የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት እየሰጡም አይደለም። ከዚህ ጋር በተያያዘ ባለፉት ዓመታት እንደ ሀገር ከተሞች በከፍተኛ ደረጃ እያደጉና እየተስፋፉ ይገኛል።

ከፍተኛ ኃይል የሚጠይቁ ትልልቅ ፎቆች በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች እየተገነቡ ሲሆን ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚጠይቁ ኢንዱስትሪዎችም በስፋት እየተገነቡ ይገኛል። በአንጻሩ የኤሌክትሪክ ኃይልን ከማመንጫ ጣቢያዎች የሚወጣውን ኃይል አስተላልፎ ወደ ተገልጋዩ ሊያደርስ የሚችለው መሰረተ ልማት ያለውን እድገት በሚሸከም መልኩ እያደገ አልመጣም። በዚህ ምክንያት በበርካታ ቦታዎች በማስተላለፊያዎች ችግር የኃይል መቆራረጥ ይገጥማል።

በተጨማሪ ደግሞ በየወቅቱ ቀላል የማይባል እንደ ስርቆት እና ውድመት ያሉ ሰሰው ሰራሽ ችግሮች በመሰረተ ልማቶች ላይ እየደረሱ የኃይል መቆራረጥ እንዲከሰት ምክንያት እየሆነ ይገኛል። በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተወሰነ መሻሻል ቢታይም የከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊያ መስመሮች ላይ የሚደርሰው ዝርፊያና ውድመት ለኃይል መቆራረጥ ምክንያት እየሆኑ ይገኛል።

እነዚህ መሰረተ ልማቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚያለማቸውና የሚያስተዳድራቸው ላይ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ስር ባሉትም የሚፈጸም ነው። በዚህ ረገድ ለኃይል መቆራረጥ ምክንያት የሆኑ በከፍተኛ የኃይል ማስተላለፊያ ምሰሶዎች ላይ የተፈጸሙ ዝርፊያና ጉዳቶች ነበሩ። ለአብነት ወደ አሶሳ በሚሄደው መስመር ላይ በተደጋጋሚ ሲከሰት የነበረውን ማስታወስ ይቻላል። ለዚህ አገልግሎቱ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የጸጥታ አካላትና ኅብረተሰቡም የሚጠበቅበትን ሊወጣ ይገባል። የኃይል መቆራረጥ ድግግሞሽንና የብልሽት ማስተካከያ ቆይታ ጊዜን ለማሳጠር አጠቃላይ ችግሮችን ለመቅረፍ በስፋት እየተሰራበት ይገኛል። ይህንንም ይበልጥ ለመቀነስ ሰፊ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ተናግረው፤ በተለያዩ አካባቢዎች የአገልግሎት አሰጣጥን የሚያሻሽሉ በርካታ ፕሮጀክቶችና የእድሳት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁመዋል። በሩብ ዓመቱ በተጣሩ የብልሹ አሠራር ጥቆማዎች መሠረት ሀያ የአገልግሎቱ ሠራተኞችን እና አመራሮች ተጠያቂ ተደርገው ጉዳያቸው በየደረጃው በሚመለከተው አካል እንዲታይ ተደርጓል።

በዚህም ከጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ጀምሮ ደመወዝ የመቁረጥ፤ ከስራ የማሰናበትና እንደ ጥፋቱ በሕግ ተጠያቂ የማድረግ ርምጃዎች ተወስደዋል። ይህም ሆኖ ከላይ ከተጠቀሱት ውጪ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በሁለት ምክንያቶች ብቻ እሱንም ለማኅበረሰቡ በማሳወቅ የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲቋረጥ የሚያደርግባቸው አጋጣሚዎች አሉ። አንደኛው እያረጁ ያሉ ኔት ወርኮችን መልሶ ለመገንባት ሰፋፊ ሜጋ ፕሮጀክቶች በየከተሞች እየተከናወኑ ይገኛል። በዚህ ወቅት በታቀደ መልኩ ኃይል የሚቋረጥ ሲሆን ይህም ለደንበኞች በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን መረጃው ተደራሽ የሚደረግ ይሆናል። ሁለተኛው በተመሳሳይ በታቀደ መልኩ የቅድመ መከላከል ስራዎች ሲከናወኑ ነባሩን ኮሪደር በመከተል የሚሰራ በመሆኑ የኃይል መቆራረጥ ይከሰታል።

ከዚህ ውጪ አንዳንድ ችግሮች ደርሰው አስቸኳይ ጥገና ማድረግ ሲያስፈልግ ለአጭር ጊዜ የሚኖር የኃይል መቆራረጥ ይኖራል። ይህም ሆኖ አንዳንዶቹ ችግሮች ከአገልግሎቱ አቅም በላይ ሲሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ችግሩን ለመቅፍ እየተሰራ ይገኛል። ባጠቃላይም የኃይል መጥፋት የቆይታ ጊዜውም ሆነ ድግግሞሹ ከዚህ በፊት ከነበረው ከፍተኛ መሻሻሎች የታዩበት ነው።

ይህም ሆኖ የኃይል መቆራረጡን በሚፈለገው ልክ ደርሷል ለማለት አያስችልም። በተጨማሪም የቅሬታ አፈታት ሥርዓቱ ወይም ምላሽ አሰጣጡ ተገልጋዮች በሚጠብቁት ልክ አለመሆኑንም እንገነዘባለን። አንዳንድ ፕሮጀክቶችም በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ አለመጠናቀቃቸው ይታወቃል። በመሆኑም በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶ እነዚህ ችግሮች መቶ በመቶ መቅረፍ ባይቻል እንኳን አፈጻጸሙ ከሕዝቡ ፍላጎትና ጥያቄ ጋር የተቀራረበ እንዲሆን በርካታ ስራዎችን ለማከናወን እቅድ ይዘን እየተንቀሳቀስን እንገኛለን።

**አዲስ ዘመን ፡- ስለነበረን ጊዜ እናመሰግናለን።**

**አቶ መሳኩ ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

# አፍሪካውያንን ያገናኘው የፋሽን መድረክ

ሰሚራ በርሀ

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ብቻ አይደለችም፤ የአፍሪካ ሕብረትና ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫም ናት። ዓለም አቀፍ ሁነቶችን ከሚያስተናግዱ ትልልቅ የዓለም ከተሞች መካከልም ትጠቀሳለች። በዚህ በጀት ዓመት ባለፉት ጥቂት ወራት ብቻ ከ20 የማያንሱ ዓለም አቀፍ ሁነቶችን ማስተናገዷም ይህንኑ ያመለክታል።

በሳምንቱ ከተካሄዱ መድረኮች አንዱ ‹‹አፍሪካ ታከብራለች›› (Africa Celebrates) የተሰኘው አንዱ ሲሆን፣ መድረኩ በተለያዩ ኩነቶች ተከብሯል።

ባሳለፍነው ሳምንት የተካሄደው ይህ መድረክ፣ በየዓመቱ የሚዘጋጅ ነው። ዋና ዓላማውም የበለጸገች አፍሪካን እውን ለማድረግ እንደ ማበረታቻ የሚዳሰሱትን በአፍሪካ የበለጸገ የጥበብ ፣ የባህል ፣ የቅርስ ፣ የንግድ እና የኢንቨስትመንት የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሽግግሮችን በማስተዋወቅ የአፍሪካን ኢኮኖሚያዊ ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ውህደት በማበረታታት የአፍሪካን በልዩነት ውስጥ ያለውን አንድነት ማክበር ነው።

የአፍሪካ ታከብራለች መድረክ የ2024 ዋና ዓላማ ከ21ኛው ክፍለ ዘመን ጋር የሚራመድ አፍሪካውያን ማስተማር ፣ ለአፍሪካውያን ብልጽግና እና ውህደት በጥበብ ፣ ባህል ፣ ቴክኖሎጂ ፣ ታሪክ እና ንግድ ላይ ጠንካራ ግንዛቤን መፍጠር የሚሉ ናቸው።

ኒቆዲሞስ የሺጥላ ‹‹ በእንደራሴ የወጣቶች ማህበር›› ውስጥ ዋና ጸሀፊ ነው። የወጣት ማህበሩ በአንድ ወጣት ሀሳብ አመንጪነት ወጣቶችን በተለያዩ መስኮች ላይ የማሳተፍ እድል በመስጠት ወጣቶች ራሳቸውን በተለያየ መስክ እንዲያበቁ የሚያደርግ ማህበር ነው›› ሲል ይገልጻል።

ማህበሩ በሲቪል ማህበረሰብ ምዝገባ እውቅና አግኝቶ ስራ ከጀመረ ሶስት ዓመታትን አስቆጥሯል።



‹‹እንደራሴ ወጣቶችን ለማንቃት እድል ይሰጣል፤ ባለው ነባራዊ ሁኔታም በኢትዮጵያም ሆነ በአፍሪካ እድሎችን እንዲያገኙ የማድረግ ስራ እየሰራ ይገኛል ›› በማለት ወጣት ኒቆዲሞስ ያብራራል።

እሱ እንዳብራራው፤ እንደራሴ በዙሪያው ያሉ ወጣቶችን ለማብቃት በሚሰራቸው ስራዎች ውስጥ ከተለያዩ ሀገር ውስጥ ከሚገኙ የወጣት ማህበራት እና ቡድኖች ጋር እንዲሁም ከአህጉረ አፍሪካ ትልልቅ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ኢትዮጵያውያን ወጣቶች የሚጠቀሙበትን እድል ይፈጥራል።

ይህ የ‹‹አፍሪካ ታከብራለች›› መድረክ በተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ውስጥ ነው የተካሄደው። የፋሽን ኤግዚቢሽን፣ የባህል ምሽት እንዲሁም የአፍሪካ ወጣቶች ፎረም በመድረኩ ተካሂደዋል።

በፋሽን ኤግዚቢሽኑ ከመላው አፍሪካ ሀገራት የተወጣጡ በርካታ ዲዛይነሮች ተሳታፊ ሆነዋል። “ ከካሜሮን፣ አልጄሪያ፣ ሞሮኮ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ናይጄሪያ እንዲሁም ከሌሎች በርካታ ሀገራት የመጡ ተሳታፊዎች ተገኝተውበታል” በማለት ያብራራው ወጣት ኒቆዲሞስ፣ አፍሪካ ለፋሽን ኢንዱስትሪው ሊውሉ የሚችሉ ከሌሎች አህጉሮች በተለየ በርካታ ባህሎች እና የደመቀ የባህል አልባሳት እንዳሏትም ተናግሯል።

የፋሽን ኤግዚቢሽኑ እነዚህን የአፍሪካ ሀገራት ማሳተፍንና አንድ ማድረግን ያለመ ሲሆን፣ ከአፍሪካውያን ውጪ ለሚገኙ ለሌሎች ዜጎችም ጭምር ማሳየትን መሆኑን አንስቷል። በፋሽን ኤግዚቢሽኑ ላይ ዲዛይነሮች የኢትዮጵያ የባህል አልባሳትን ይዘው ቀርበዋል። ከተፈጥሯዊ ግብዓቶች የተዘጋጁ እና ሙሉ ለሙሉ የእደ-ጥበብ ውጤት የሆኑ፣ ከቆዳ የተሰሩ ቦርሳዎችን እንዲሁም ሌሎች የውበት መጠበቂያ ምርቶችን ከመላው አፍሪካ ይዘው የቀረቡ ተሳታፊዎችን በኤግዚቢሽኑ ላይ ተመልክተናል።

በአፍሪካ እና በአፍሪካውያን የተሰሩ አልባሳትን፣ የምግብ አይነቶችን፣ የኪነጥበብ ስራዎችን ማበረታትን ዓላማው ያደረገው ይህ የአፍሪካ ታከብራለች ክንውን፣ የአፍሪካን የንግድ ልውውጥ እና ቱሪዝምን መደገፍ፣ ሴቶች እና ወጣቶችን ማብቃትንም ዓላማው ያደረገ ነው።

ባለፉት ጊዜያት “የአፍሪካ ታከብራለች” የፋሽን ኤግዚቢሽኖች 38 የሚጠጉ የአፍሪካ ሀገራት የተሳተፉባቸው ስለመሆናቸው የአፍሪካ ሰለብሬት ይፋዊ ድህረ ገጽ የጠቆመ ሲሆን፣ 11 የሚሆኑ ከአፍሪካ ውጪ የሚገኙ ሀገራትም በፋሽን ኤግዚቢሽኑ ላይ መሳተፋቸውን አስታውቋል።

በሰሞኑ የፋሽን ኤግዚቢሽን ላይ ስራቸውን ይዘው ከቀረቡት ውስጥ እታገኝ እንግዳወርቅ አንዷ ናት። እታገኝ “ ፒፖስ ፋሽን ” የተሰኘ የራሷ የፋሽን ብራንድ አላት። በዲዛይን ስራ አምስት ዓመት ያህል የቆየች ሲሆን፣ የአፍሪካውያን ጨርቅን ከኢትዮጵያውያን የባህል ልብስ ጋር በማጣመር የዲዛይን ስራዎቿን ለደንበኞቿ ታቀርባለች።

“በዚህ ኤግዚቢሽን ላይ ስሳተፍ የመጀመሪያዬ ነው። አንድ ቦታ ላይ ብቻ ሆኖ ከመስራት እንዲዚህ አይነት ዝግጅቶች ላይ መገኘት ራስን ለማስተዋወቅ ጥሩ አጋጣሚን ይፈጥራል። ” የምትለው እታገኝ፣ የምትሰራቸው ልብሶች በአብዛኛው በአፍሪካውያን ዘንድ የተለመዱ እና አይን ያዝ የሚያደርጉ የሚማርኩ ቀለማት ያላቸው መሆናቸውን አስታውቃለች፡፡

ሁነቱን ከምትሰራው ስራ ጋር የተጣጣመ ሆኖ አግኝታዋለች። ኢትዮጵያዊ ሆና በብዛት የአፍሪካውያን የባህል አልባሳት ይዛ መቅረቧ ከጎብኚዎች የተለያዩ አስተያየቶች እንዲሰጣት ማድረጉንም ገልጻለች። “ አፍሪካውያን የራሳቸውን አልባሳት ይዘን ሲያዩን በጣም ደስ ይላቸዋል። አንዳንዶች ደግሞ አልባሳቱን እኛ የምናዘጋጃቸው አይመስላቸውም፤ ከአፍሪካ ሀገሮች አምጥተን የምንሸጥ ይመስላቸዋል ” ስትልም አብራርታለች።

ወደ አፍሪካ ፊቴን አዞሬ የአፍሪካ ጨርቆችን ዲዛይን ማድረግ ከጀመርኩ አምስት ዓመት ሆኖኛል ስትል ጠቅሳ፣ አቀባበላቸው ጥሩ መሆኑንም ትገልጻለች። ‹‹ስራውን ስጀምረው አንዳንድ የአምባሳደር ባለቤቶች ደንበኞቼ ወደውት ጨርቁን ከሀገራቸው እያመጡልኝ እሰራ ነበር፤ አሁን አሁን ብዙ ሰው ይፈልገዋል ትላለች።

በዚህ የፋሽን ኤግዚቢሽን መድረክ ላይ መገኘቷ ከሰዎች ጋር አድራሻ ለመለዋወጥ፣ ምርቶቿን ለመሸጥ እና ሌላ ጊዜ ልታገኛቸው የማትችላቸውን ደንበኞች ማግኘት እንዳስቻላትና በጣም ጥሩ መድረክ ሆኖ እንዳገኘችው ገልጻለች።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## የኅዳር በሽታ እንዳይለምድብን!

ዋሰልኝ አየለ

በተለምዶ ‹‹የሕዳር በሽታ›› እየተባለ የሚጠራ በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የተከሰተ ወረርሽኝ ነበር። ይህ የሆነው ከመቶ ምናምን ዓመታት በፊት ነው። በዘመኑ እንደ አሁኑ የረቀቀ የመመርመሪያ ቴክኖሎጂ የለም። ክስተቱ እንደ ቁጣ (መለኮታዊ ኃይል) ተደርጎ ነው የሚታየው። የሕዳር በሽታ የተባለው ደግሞ የተከሰተው በሕዳር ወር ስለሆነ ነው። በዚህም ምክንያት ‹‹ሕዳር ሲታጠን›› የሚባል ልማድ አለ። ለምን በሕዳር ወር ሆነ? የሚለውን ጥያቄ በአሁኑ ዘመን ጥናት ማወቅ እንችላለን፡፡

ባለፈው ዓመትም፣ በዚህ ዓመትም (ከሳምንት በፊት) የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት መግለጫ ሰጥቶ ነበር። የጤና ተቋማትና ማኅበራት ጥናታዊ ማብራሪያዎችንም ተናግረዋል። በተለይ ባለፈው ዓመት በሰጡት ማስጠንቀቂያና ሰፊ ማብራሪያ እንደተገለጸው፤ የጥቅምት እና የሕዳር ወር ጉንፋን መሰል ሕመሞች ይታዩበታል። ጤና ሚኒስቴር ከኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ጋር በጋራ በመሆን በሁለት ሺህ ያህል ናሙናዎች ላይ ምርመራ አድርጎ፤ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ አካባቢዎች የጉንፋንና ኢንፍሉዌንዛ በሽታ መከሰቱን ይፋ አድርጎ ነበር። እነሆ ዘንድሮም መሰል ሕመም በብዙዎች ላይ እየታየ ነው።

ለጉንፋን መሰል ክስተቶች ምክንያት የተባለውም፤ የዝናብ ወራት ማለፉን ተከትሎ በጥቅምትና ሕዳር ወቅት ላይ አብዛኛውን ጊዜ የጉንፋንና ኢንፍሉዌንዛ በሽታ የሚከሰት መሆኑ ነው። ከጥናቱ ባሻገር ሁላችንም በየአቅራቢያችን እንደምናስተውለው ሰሞኑን ብዙ ሰው የጉንፋን መሰል ሕመሞች ገጥሞታል። ይህ ክስተት በዚህ ዓመት ብቻ የተስተዋለ ሳይሆን የጥቅምትና ሕዳር ወራት ላይ በየዓመቱ የሚታይ ነው።

ትዝብታችን እዚህ ላይ ነው። የጤና ተቋማትና የጤና ባለሙያዎች ማኅበራት ለእንዲህ አይነት ክስተቶች ‹‹መከላከያ›› ብለው ያስቀመጧቸው ነገሮች አብዛኞቹ የማንተገብራቸው ናቸው። በዚህም ምክንያት በዓመቱ ጥቅምትና ሕዳር ወር ላይ የእንዲህ አይነት ክስተቶች ተጠቂ እንሆናለን። የወቅት መፈራረቅ የአየርን ሁኔታ መቀየሩ በኢትዮጵያ ብቻ ያለ ክስተት አይደለም፤ ዳሩ ግን የሰለጠኑት አገራት ሰው ሰራሽ በሆነው ጥበብ ይከላከሉታል፡፡

ተፈጥሮ ነውና ክረምት ተራውን ለመኸር ወቅት ይለቃል። በዚህን ጊዜ ብዙ አበቦች ይፈነዳሉ፣ ብዙ የዕፅዋት አይነቶች ያፈራሉ። ይህ ክስተት የአየር ለውጥ ያመጣል። በክረምት ውሃ የሞሉ ወንዞች መድረቅ ይጀምራሉ። እስከ ጥቅምት መጨረሻ መቆየት የቻሉ ወንዞችና ኩሬዎች ካሉ፤ ሕዳር ላይ ይደርቃሉ። ውሃ ያጠራቀሙ ቦታዎች ሁሉ ሲደርቁ ሌላ ሽታ ይፈጠራል።

እነዚህ ከላይ የተገለጹት የተፈጥሮ ክስተቶች ወደ በሽታነት የተቀየሩት በእኛ በሰዎች ጥፋት ነው። ውሃ ይዘው የነበሩ ቦታዎች ላይ ቆሻሻ እንጥላለን፤ ውሃው ሲደርቅ መጥፎ ሽታ ይፈጥራል። እንደሚታወቀው ውሃ በተፈጥሮ ብቻውን ሽታ የለውም። የሚረብሽ ሽታ እንዲኖረው አድርገን ያበላሸነው እኛ ሰዎች ነን። በክረምትና በመኸር ወቅት ላይ ያለውን የአየር መለዋወጥ በቴክኖሎጂ ማስተካከል ባንችል እንኳን ቢያንስ በቀላሉ ባለመበከል መከላከል እንችል ነበር፤ ዳሩ ግን እዚህ ደረጃ ላይ ባለመድረሳችን የሕዳር በሽታ በዚህ ዘመንም እየደገመን ነው።

የጤና ተቋማቱ መከላከያ ብለው ካስቀመጧቸው ነገሮች ውስጥ ሌላው ደግሞ የግልና የአካባቢን ንጽህና መጠበቅ ነው። ለአንደኛ እና ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ሊነገር የሚገባውን የግልና የአካባቢ ንፅህና ጉዳይ ከዲግሪ በላይ የትምህርት ደረጃ ላለው ማህበረሰብ ማስተማር ምን ያህል ገና ብዙ እንደሚቀረን ያሳያል። ምክንያቱም ይህ ችግር እየተፈጠረ ያለው የተማሩ በሚባለው የኅብረተሰብ ክፍሎች ጭምር ነው። በትልልቅ ተቋማት ውስጥ የምናያቸው ችግሮች አሳዛኝ ናቸው። እነዚያ ተቋማት ውስጥ ያሉት ግን የተማሩ የሚባሉ ሰዎች ናቸው።

ጉንፋን እና መሰል በሽታዎች የሚከሰቱት ከመጥፎ ሽታ ነው። እነዚህ መጥፎ ሽታዎች የሚፈጠሩት ደግሞ ካለማወቅ ሳይሆን ከከፍኛ ቸልተኝነት ነው። አልኮል ጠጥቶ ትራንስፖርት ውስጥ የሚገባ ሰው ሊረብሽ እንደሚችል አይጠፋውም። የጫማውን ንጽህና የማይጠብቅ ሰው ጫማ መጥፎ ሽታ እንደሚፈጥር አይጠፋውም። ይህ መጥፎ ሽታ ጉንፋን እና ሌሎች ተዛማጅ በሽታዎችን እንደሚያመጣ አይጠፋውም፤ ዳሩ ግን እነዚህ ሁሉ የሚሆኑት በከፍተኛ ቸልተኝነት ነው።

ምንም እንኳን የወንዞች ዳርቻ ፕሮጀክቶች አዲስ አበባን ውብ እና ጽዱ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ላይ ቢሆኑም፤ ዳሩ ግን ዋናው ለውጥ መምጣት ያለበት የሰዎች ጭንቅላት ላይ ነው። አሁንም ድረስ ብዙ የወንዝ ዳርቻዎች አፍንጫ ተይዞ የሚታለፉ ናቸው። ራስ የሚያዞር መጥፎ ሽታ ያላቸው ናቸው። ያ መጥፎ ሽታ የተፈጠረው በክረምቱ ወቅት የወረደው ዝናብ ቆሻሻ ሆኖ ሳይሆን እኛ ሰዎች በክለነው ነው። በተጠራቀመው የዝናብ ውሃ ላይ ሌላ ባዕድ ነገር ቀላቅለንበት ነው። ብዙ ሰዎች ደረቅም ሆነ ፍሳሽ ቆሻሻ የሚጥሉት ወንዝ መሰል ነገር ውስጥ ነው።

የግዴለሽነታችን ነገር በጣም አሳሳቢ ነው። እንኳን እንዲህ ክረምትና መኸር የሚቀያየርበት ወቅት በዋናው ክረምት ወይም የበጋ ወቅት ራሱ አስቸጋሪ ነው። በአንፃራዊነት ሙሉ ክረምት ሳይሻል አይቀርም። በእንዲህ አይነቱ ወቅት ብዙ መጥፎ ሽታዎች አሉ። በተፈጥሮ የተጠራቀመው እንዳለ ሆኖ፤ ሌሎች ተጨማሪ ነገሮች ደግሞ ችግሩን ያባብሱታል። ከእነዚህም አንዱ በየሰፈሩ የሚሰበሰብ ቆሻሻ ነው፡፡


በብዙ አካባቢዎች እንዳስተዋልኩት በሳምንቱ ውስጥ የተወሰኑ ቀናት (ለምሳሌ እሁድ፣ ረቡዕ እና ዓርብ) በየአካባቢው ያሉ የተሰበሰቡ ቆሻሻዎች የሚነሱበት ሊሆን ይችላል። እነዚህ ቀናት የማንሻ መሆናቸውን የየአካባቢው ነዋሪ ያውቃል። ይሄ ብቻ አይደለም፤ በዕለቱ የሚያነሱ ሰዎች ሲመጡ በጡሩንባ ‹‹ቆሻሻ አውጡ!›› እየተባለ በከፍተኛ ጩኸት ይነገራል። እንዲያውም አንዳንድ ቀን እየተበሳጨሁ ‹‹አንዴ ከተነገረ አይበቃም እንዴ!›› ብዬ በውስጤ እገረማለሁ። ለካ ወደው አይደለም።

አሳዛኙ ነገር ያ ሁሉ ጩኸት ተጮሆ ቆሻሻ የማያወጡ ሰዎች አሉ። ልክ አንሽዎች አንስተው ሲሄዱ ከየት እንደመጡ ሳታውቅ ቆሻሻ ጥለው ይሄዳሉ። እነዚህ ሰዎች እንግዲህ ሊቀጡ ይገባ ነበር። ሲጀመር የቆሻሻ ማንሻ ቀናትን ማወቅ ነበረባቸው፤ እሱም ይረሳል እንበል፤ ለማስታወስ ተብሎ ያን ያህል አካባቢው እስከሚናወጥ ቅስቀሳ ሲደረግ ማውጣት ነበረባቸው። እሱንም ሳይሰሙ ቀሩ እንበል፤ ቢያንስ ምናለ በሚቀጥለው ቀን የሚያነሱት ሲመጡ ቢያወጡት? እንዲያው ምናልባት ሆን ብለው ይሆን?

በሱፍ እና ከረቫት ዝንጥ ብሎ የለበሰ ሰው ያለምንም መሸማቀቅ መንገድ ዳር የተጠቀመበትን ሶፍት ይጥላል። ይሄ ለዚያውም ቀላሉ ነው፤ ከዋናው አስፋልት ገለል ብሎ ሽንቱን የሚሸናው ማንም ሰው የሚታዘበው ነው። የግንብ ጥግ ሆኖ መጥፎ ሽታ የሌለው ላይገኝ ነው ማለት ነው። የውሃ ማፋሰሻዎች ሽንት ጭምር ነው የሚያፈሱት ማለት ነው።

ታዲያ በዚህ ሁኔታ በሕዳር ብቻ ሳይሆን ዓመቱን ሙሉ ጉንፋን ቢይዘን ምን ይገርማል? እንዴት በሽታ እንኳን አያስተምረንም? የሕዳር በሽታ እንዳይለምድብን አሁንም ቀልብ እንግዛ!

# ዓለም አቀፍ



## የዶናልድ ትራምፕ መንግሥት ትኩረቱን በሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት ማስቆም እንጂ በኃይል የተያዙ ቦታዎች ላይ አያደርግም ተባለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የዶናልድ ትራምፕ መንግሥት ትኩረቱን በሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት ማስቆም እንጂ በኃይል የተያዙ ቦታዎች ላይ አያደርግም ተባለ፡፡

ለአንድ ሳምንት ተብሎ የተጀመረው የሩሲያ -ዩክሬን ጦርነት ሶስተኛ ዓመቱ ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ አሜሪካ ለዩክሬን ከፍተኛ የገንዘብ እና ጦር መሳሪያ ድጋፍ ከሚያደርጉ ሀገራት መካከል ዋነኛዋ ናት፡፡

አሜሪካ እስካሁን 64 ቢሊዮን ዶላር ለዩክሬን ድጋፍ ደረገች ሲሆን፤ ይህ ገንዘብ በአሜሪካዊያን ህይወት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማድረሱን ተከትሎ የምርጫ መከራከሪያ አጀንዳ ሆኗል፡፡

ይህን ተከትሎ ዶናልድ ትራምፕ የዩክሬን ጦርነት የምርጫ ቅስቀሳ አጀንዳ ያደረጉት ሲሆን፤ ጦርነቱን አንድ ቀን አስቆመዋለሁ ሲሉ በተደጋጋሚ ተናግረዋል፡፡

የምርጫ ቅስቀሳቸው ለውጥ አምጥቶም ዶናልድ ትራምፕ ምርጫውን ማሸነፋቸው ይፋ የሆነ ሲሆን የፊታችን ጥር ወር ላይ ስልጣን ይረከባሉ፡፡

ይሁንና ፕሬዚዳንቱ ስልጣን ከመረከባቸው በፊት ስለ ዩክሬን-ሩሲያ ጦርነት መቆም ጉዳይ እየሰሩበት እንደሆነ ዩሮ ኒውስ ዘግቧል፡፡

የሪፐብሊካን ፓርቲ ዋና ስልት ነዳፊ እና የዶናልድ ትራምፕ ምርጫ ቅስቀሳ ቡድን አባል የነበሩት ብሪያን ላንዛ እንዳሉት፤ አዲሱ የዶናልድ ትራምፕ አስተዳደር በኃይል ስለተወሰዱ የዩክሬን ግዛቶች አያተኩርም ብለዋል፡፡

የዶናልድ ትራምፕ አስተዳደር የሚያተኩረው ሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነቱን እንዲያቆሙ ማድረግ ነው ያሉት ብሪያን፤ እንደ ክሪሚያ ያሉ ቦታዎች ወደ ሩሲያ ተካለዋል ብለዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ሩሲያም ሆነ የዩክሬን ጦር አሁን ባሉበት ሆነው ከአንድ ሺህ በላይ ኪሎ ሜትር ርቀት ከሁለቱም ተፋላሚዎች ነጻ ሆኖ እንዲቆይ የሚል እቅድም ቀርቧል፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ ሩሲያ ከአሜሪካ ባለስልጣናት ጋር በመነጋገር ላይ መሆኗን የሀገሪቱ ምክትል ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጊ ሪያብኮቭ ተናግረዋል፡፡

የዩክሬን ፕሬዚዳንት ቮሎዶሚር ዘለንስኪ ሩሲያ በኃይል ከያዘቻቸው የዩክሬን ግዛቶች ጦሯን ካላስወጣች ሰላም እንደማይሰፍን በተደጋጋሚ መናገራቸው አይዘነጋም፡፡



## ኳታር የሀማስ ኃላፊዎችን ከዶሃ ለማስወጣት ተስማማች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ኳታር በሀገሪቱ የሚኖሩ ከፍተኛ የሀማስ አመራሮችን ለማስወጣት ከአሜሪካ የቀረበላትን ጥያቄ መቀበሏ ተሰማ፡፡

ሀማስ በ2012 በሶርያ የእርስ በእርስ ግጭት መቀስቀሱን ተከትሎ ዋና ቢሮውን ከደማስቆ ወደ ዶሃ አዘዋውሯል፡፡

የጥቅምት ሰባቱን ጥቃት ተከትሎ አሜሪካ “ኳታር በተለመደው መንገድ ከቡድኑ ጋር ግንኙነቷን መቀጠል እንደማትችል” ስታስጠነቅቅ ሰንብታለች፡፡

ሀገሪቱ በዶሃ የሚገኘውን የቡድኑን ዋና ቢሮ እንድትዘጋ እና ለኃላፊዎቹ ጥገኝነት ከመስጠት እንድትቆጠብ ጫና ስታደርግ መቆየቷን ሲኤንኤን የአሜሪካ እና ኳታር ምንጮቹን ጠቅሶ ዘግቧል፡፡

ዘገባው ሀማስ ታጋቾችን ለመልቀቅ እና የሰላም ስምምነት ላይ ለመድረስ የቀረበለትን ተደጋጋሚ ጥያቄ ውድቅ ማድረጉን ተከትሎ፤ መሪዎቹ በማንኛውም የአሜሪካ አጋር ዋና ከተሞች ተቀባይነት ሊያገኙ አይገባም የሚል ሃሳብ በዋሽንግተን በኩል መንጸባረቁን ጠቅሷል፡፡

ሀማስ በነሐሴ ወር ሄርሽ ጎልድበርግ የተባለ ግለሰብን ጨምሮ አምስት የአሜሪካ ዜግነት ያላቸውን ታጋቾችን ከገደለ በኋላ ከዋሽግተን የበረታው ግፊት ኳታር ኃላፊዎቹን ለማስወጣት የቀረበላትን ጥያቄ እንድትቀበል እንዳደረጋት ነው የተነገረው፡፡

አሜሪካ ከሁለት ሳምንት በፊት ኳታር መሪዎቹን እንድታስወጣ በጠየቀችው መሰረት ኳታር ከሳምንት በፊት ባለስልጣናቱ ከሀገሪቷ ለቀው እንዲወጡ ትእዛዝ ሰጥታለች፡፡

በዚህም መሰረት የሀማስ ወቅታዊ መሪ ካሊድ ማሻልን ጨምሮ ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናት በቅርቡ ዶሀን ለቀው እንዲወጡ ሊደረግ ይችላል፡፡

ከፍተኛ አመራሮቹ ሀገሪቷን ለቅቀው ለመውጣት እስከ መቼ ጊዜ እንደተሰጣቸው እና ቀጣይ የሚያርፉበት ሀገር የት ሊሆን እንደሚችል የታወቀ ነገር የለም፡፡

ነገር ግን ቱርክ፣ ኢራን፣ ሊባኖስ እና አልጄሪያ ቀጣዮቹ የሀማስ መሪዎች መጠጊያ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡

በተጨማሪም የጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ ጽህፈት ቤት ኳታር የሃማስ የባንክ ሂሳቦችን እንድታግድ እና የባለስልጣናቱን ንብረት እንድትይዝ ጠይቋል።

ከጉዳዩ ጋር በተገናኘ ሀማስ በአንድ ከፍተኛ ባለስልጣኑ በኩል በሰጠው ምላሽ “አመራሮቹን ከኳታር ማስወጣትን በተመለከተ እየተናፈሰ የሚገኘው መረጃ መሰረተ ቢስ እና በቡድኑ ላይ ጫና የመፍጠር ስልት ነው” ብሏል። ከዚህ ቀደምም የሃማስ መሪዎች ከዶሃ ሊወጡ ነው የሚሉ በትክክለኛ መረጃ ያልተደገፉ ዘገባዎች ሲወጡ መቆየታቸውን በማስታወስ።

ባለፈው አንድ ዓመት በእስራኤል እና ሀማስ መካከል የተኩስ አቁም ስምምነት እንዲደረስ ዋና ተዋናይ ሆና የቆየችው ኳታር ከዚህ ውሳኔ በኋላ በድርድሩ የሚኖራት ሚና ጥያቄ ውስጥ ገብቷል፡፡

ዶሃ ከ2012 ጀምሮ የሃማስ የፖለቲካ ቢሮ መቀመጫ ከመሆን ባሻገር ከ2018 ጀምሮ በእስራኤል እና አሜሪካ እውቅና ጋዛን ለሚያስተዳድረው ሀማስ ለሠራተኞች ደመወዝ በሚል በየወሩ 15 ሚሊዮን ዶላር ትሰጣለች፡፡

# ስፖርት

# ‹‹የአፍሪካ ዋንጫን ለማዘጋጀት ስልታዊ እቅድ ያስፈልጋል››

## - ኢንስትራክተር ሰለሞን ገብረስላሴ

**ዓለማየሁ ግዛው**


ኢትዮጵያ የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ)ን ከመሰረቱ ሀገራት አንዷ ብትሆንም አህጉራዊ ውድድሩን ካዘጋጀች ግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ አስቆጥራለች። በመድረኩ በየጊዜው መሳተፍም ከብዷታል። ወደ ውድድሩን አዘጋጅነት ለመመለስ ግን በቅርቡ ለካፍ ጥያቄ ማቅረቧ ይታወቃል።

የኢትዮጵያ የ2029 አፍሪካ ዋንጫ አዘጋጅነት ጥያቄ ተቀባይነት ካገኘ ከመሰረተ ልማት ጀምሮ በርካታ መሟላት ያለባቸው ጉዳዮች አሉ። ይህንን በተመለከተም የተለያዩ ባለሙያዎች አስተያየታቸውን እየሰነዘሩ ይገኛሉ። ውድድሩን በተሳካ ሁኔታ ለማዘጋጀት ስልታዊ እቅድ ተነድፎ በትኩረት መስራት እንደሚያስፈልግ ከሚናገሩ ባለሙያዎች አንዱ የእግር ኳስ ዳኞች ኢንስትራክተር ሰለሞን ገብረስላሴ ናቸው።

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ በባለሙያነት፣ በዳኝነትና በኃላፊነት ደረጃዎች ያገለገሉት ኢንስትራክተር ሰለሞን፤ በአሁኑ ወቅት በካፍና ፊፋ ኮሚሽነርነትና የኢትዮጵያ ዳኞች ኢንስትራክተር ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ። ኢትዮጵያ የ2029 የአፍሪካ ዋንጫን ለማዘጋጀት በማቀዷ እንደ እግር ኳስ ባለሙያ መደሰታቸውን የሚናገሩት ኢንስትራክተር ሰለሞን፤ በእግር ኳስ ውስጥ በዳኝነት እና በሌሎች ትልልቅ ደረጃዎች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫን እንድታዘጋጅ አብዝተው ይመኙ እንደነበር ይገልጻሉ። ኢትዮጵያ የአፍሪካ እግር ኳስ መስራች እንደመሆኗ ውድድሩን በተሳካ ሁኔታ ማስተናገድ ብዙ ሀብት፣ በርካታ ባለሙያዎች እንደሚያስፈልጉ ጠቁመው፤ መንግሥት ለዚህም ትኩረት መስጠት እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡

እንደ እሳቸው አስተያየት፤ የአፍሪካ ዋንጫን ለማስተናገድ ከሚያስፈልጉት መሠረታዊ ነገሮች መካከል ስድስት ደረጃቸውን የጠበቁ ስታድየሞች እና ለልምምድ የሚሆኑ ሜዳዎች ወሳኝ ናቸው። ከመሰረተ ልማት አኳያ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ ስታድየሞች ቁጥር ውድድሩን ለማስተናገድ ከበቂ በላይ ናቸው። ይሁን እንጂ ደረጃቸውን ለማሻሻል ብዙ ስራ ያስፈልጋል። ይህንን ለመስራትም መንግሥት ቁርጠኝነቱን አሳይቶ እየሰራና አንዳንድ ስታድየሞች እያደሰ ይገኛል፡፡ ውድድሩን ለማዘጋጀትና የሚያስፈልጉትን መሰረተ ልማቶች ለማሟላት የሚቀረው ጊዜ በቂ በመሆኑ፣ በዚህ ጊዜ በጅምር ላይ የሚገኙትን ስታድየሞችን አጠናቆ ውጤታማ ዝግጅት ማድረግ ይቻላል፡፡ ስኬታማ ውድድር ለማዘጋጀትና እድሉን ለመጠቀም ግን ሁሉም በሙያው መረባረብ አለበት፡፡

መንግሥት ከአምስት ዓመት በኋላ ውድድሩን ለማዘጋጀት ቁርጠኝነቱን ከማሳየት በተጨማሪ፣ ዝርዝር የስራ እቅድ ያዘጋጃል የሚል ተስፋ እንዳላቸው ኢንስትራክተር ሰለሞን ይናገራሉ። ለዚህም ብዙ ባለሙያዎችን አቅፎ የሚንቀሳቀስ ብሔራዊ የአምስት ዓመት ስልታዊ እቅድ ማዘጋጀት አለበት ይላሉ። ይህም ከወዲሁ እቅዶችን በማውጣት በዛ መሰረት መስራት የሚቻል ከሆነ ውድድሩን የማስተናገድ እድሉን ማሳካት ይቻላል ባይ ናቸው።



ፎቶ - አዩብ ተፈሪ

ይህንን እውን ለማድረግም በመንግሥት፣ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር፣ እግር ኳስ ፌዴሬሽንና በባለሙያዎች መካከል ጠንካራ የጋራ ትስስር ፈጥሮ በቅንጅት መስራት ይጠይቃል ይላሉ፡፡ "ስኬታማ ውድድር ለማዘጋጀት በባለሙያዎች መካከል በእቅድ የተደገፈ ቅንጅታዊ ስራ ከወዲሁ መሰራት" አለበት የሚሉት ኢንስትራክተር ሰለሞን፤ በዚህም መሰረት ማን ምን ይሰራል፣ መቼ እና እንዴት የሚሉት ጉዳዮች በእቅዱ ውስጥ ተካተው የጋራ ክንውንና ግምገማ ማድረግ አስፈላጊ ነው ይላሉ፡፡ እግር ኳሱ የሚመለከታቸው አካላትም ለዚህ እጅ ለእጅ ተያይዘው በአንድነት ሊሰሩ እንደሚገባ አስረድተዋል።

እንደ ኢንስትራክተር ሰለሞን ሃሳብ፣ ካፍ ውድድሩን የማስተናገድ እድል ሲሰጥ የዝግጅት ሁኔታውን ደረጃ በደረጃ የሚከታተልበትና የሚገመግምበት ሥርዓት አለው። ለዚያም የሚመጥን ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ የግድ ነው። ከመሠረተ ልማት፣ ሆቴል፣ ትራንስፖርትና እግር ኳስ ሜዳዎችን ከማሟላት ጋር መስፈርቱን በትክክል ለማሟላት ዝግጅቱ የግድ በባለሙያዎች ድጋፍ መታገዝ አለበት። ለዚህም መንግሥት ቁርጠኛ መሆን አለበት።

እግር ኳስ በዓለም ተወዳጅና የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርን ለመፍጠር ከፍተኛ ሚናን የሚጫወት ስፖርት እንደመሆኑ፤ ኢትዮጵያ ውድድሩን በማስተናገዷ፣ የተሟላ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራን፣ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን፣ የመሰረተ ልማት ግንባታ እና የሀገር ገጽታ ግንባታን ለመፍጠር ቁልፍ ሚናን ስለሚጫወት እድሉ ከተገኘ በአግባቡ ልንጠቀምበት እንደሚገባ ኢንስትራክተር ሰለሞን ያስረዳሉ።

ውድድሩን ለማዘጋጀት ከሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች ጎን ለጎን ጠንካራና ተፎካካሪ ብሔራዊ ቡድን ለመገንባትም ከፍተኛ ጥረት እንደሚጠበቅ የሚናገሩት ኢንስትራክተር ሰለሞን፤ በሁሉም አካባቢዎች የእግር ኳስ ልማት ስራዎችን ለማስፋፋት የሚደረገው ስራ ተጠናክሮ ተፎካካሪ ብሔራዊ ቡድን የመገንባት እንቅስቃሴ መጀመር ይኖርበታል ይላሉ። ለዚህም የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግንና ሌሎች የሊግ ውድድሮች ጠንካራ እንዲሆን በማድረግ ምርጥ ተጫዋቾችን ማፍራት ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ እምነታቸው ነው።